# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ፣የቋንቋዎች ጥናት የጆርናሊዝምና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

## የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር


**የግለመር የመማር ዘዴ አማርኛ ቋንቋን አንብቦ ከመረዳት ችሎታ ጋር ያለው ተዛምዶ መፈተሽ፤ በሀዲያ ዞን በምዕራብ ባዳዋቾ ወረዳ ጃርሶ ኦንጆጆ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት**


በ

አበበ ታሪኩ ጣራሞ



አዲስ አበባ

ነሀሴ 2016 ዓ.ም

# የግለመር የመማር ዘዴ አማርኛ ቋንቋን አንብቦ ከመረዳት ችሎታ ጋር ያለው ተዛምዶ መፈተሽ፤ በሀዲያ ዞን በምዕራብ ባዳዋቾ ወረዳ ጃርሶ ኦንጆጆ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት


አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣የቋንቋዎች ጥናት የጆርናሊዝምና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት


የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

አማርኛን በማስተማር የኤ.ም. ኤ ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት


በ

አበበ ታሪኩ

ለአማከሪ

ግርማ መንግስቱ ዶ/ር


አዲስ አበባ

ነሀሴ 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣የቋንቋዎች ጥናት የጆርናሊዝምና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

# የግለመር የመማር ዘዴ አማርኛ ቋንቋን አንብቦ ከመረዳት ችሎታ ጋር ያለው ተዛምዶ መፈተሽ፤ በሀዲያ ዞን በምዕራብ ባዳዋቾ ወረዳ ጃርሶ አንጆጆ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት

አማርኛን በማስተማር የኤ.ም.ኤዲግሪ ከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ

በ

አበበ ታሪኩ

ለአማከሪ

ግርማ መንግስቱ ዶ/ር

# በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የግለመር መማር ዘዴ አንብቦ ከመረዳት ችሎታ ጋር ያለው ተዛምዶ መፈተሽ 9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት

በ

አበበ ታሪኩ

**የፈተና ቦርድ አባለት**

**አማካሪ................................ፊርማ ...................... ቀን............................**

**የውጭ ፈተኝ.........................ፊርማ...................... ቀን...........................**

**የውስጥ ፈተኝ.......................ፊርማ ..................... ቀን ..........................**

## ማረጋገጫ

ይህ የጥናት ጽሁፍ የእኔ መሆኑን ለጥናታዊ ጽሁፍ ግብአት እንዲሆን ተግበራዊ የሆኑ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ የሉት ድርሳናት ዋቢነታቸው በትክክል የተጠቀሰ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም ፣ አበበ ታሪኩ

ፊርማ ፣____________________________

ቦታ ፤ የሂዩማኒቲ ፣የቋንቋዎች ጥናት የጆርናሊዝምና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ሥነ- ጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት አዲስ አበባ

# ምስጋና

በቅድሚያ ስለ ሁሉ እግዚአብሔር ይመስገን ። በየትኛውም ሰዓት ውድ ጊዜአቸውን ሰውተው የማቀርብላቸውን ረቂቅ ፅሁፍ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ በጥልቀት በማንበብ አስፈላጊውን ድጋፍናእርማት በመስጠት ቃላቱና ሀረጋቱን በማቃናት በጥናቱ ወረቀት ውስጥ የቀረቡት ይዘቶች መልካም መልዕክቶችን እንዲይዙ በማድረግና የጥናታዊ ፅሁፍን ምንነትና አሰራር ስርዓትን ተከትዬ እንድሰራ አቅጣጫ በማሳየት ከፍተኛ ሙያዊ ድጋፍ ለላገሱልኝ አማካሪዬ ዶ/ር ግርማ መንግስቱ እና የገንዘብ ድጋፍ ለደረገው አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ልባዊ ምስጋና አቀርባለሁ ።

ይህ ጥናት ከግብ ይደርስ ዘንድ አስፈላጊውን መረጃ በመስጠት የተባበራችሁኝ ፣ የጥናቱን ፅሁፍ ያለመሰልቸት በማንበብ ጠቃሚ አስተያየትና ምክር በመስጠት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለዚህ ጥናት መሳካት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ላበረከተችሁ ጓደኞቼ ፣ ሁሉ ምስጋናየ ይድረሳችሁ ።

በመጨረሻም ጥናቴን ከጀመርኩበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ሚጠናቀቅበት ጊዜ ድረስ በማበረታታትና በመደገፍ ከጎኔ ለሆነችልኝ ለውድ ባለቤቴ ለወ/ሮ አምሳሉ ሚቶሬ የላቀ ምስጋናዬ ይድረስሽ እላለሁ።

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት ዋና ተግባር በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የግለ መር መማር ዘዴ አንብቦ ከመረዳት ችሎታ ጋር ያለውን ተዛምዶ መፈተሽ ሲሆን ፣ ይህንን አላማ ከዳር ለማድረስ ጥናቱ ተዛምዷዊ የምርምር ንድፍን ተከትሏል ። በሀዲያ ዞን በምዕራብ በደዋቾ ወረዳ ጆርሶ ኦንጆጆ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአመቺ የናሙና አመራረጥ ዘዴ ተመርጧል ። የጥናቱ ተሳታፊዎች የጆርሶ ኦንጆጆ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት በ2015 ዓ.ም የሚማሩ በአመቺ ናሙና የተመረጡ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ሲሆኑ፣ጥናቱ የተከተለው ቅንጅታዊ የምርምር ዘዴን ነው በፅሁፍ መጠይቅ እና በአንብቦ መረዳት ፈተና ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ ግብአቶች ተሰብሰበውና ተጠናቅረው በመጠናዊ የምርምር ዘዴ በሆነው በድብልቅ የአተናተን ስልት ተተንትኖ ቀርቧል። ትንተናውን ለማካሄድ SPSS Software ተግባራዊ ሆኖዋል፡፡ የጥናቱ ውጤት ተማሪዎች ንዑሳን የግለ መር መማር ዘዴዎችን ግብ ማስቀመጥ፣የመማር ፍላጎትና የመማር ዘዴ እንደሚጠቀሙ አመልክቷዋል ። በግለመር መማር ዘዴና አንብቦ በመረዳት ችሎታ መካከል አዎንታዊ የሆነ ግኑኝነት እንዳለም የጥናቱ ውጤት አማልክቷል ። ሌላው ግለ መር የመማር ዘዴዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታን የማሳደግ ድርሻቸው ከፍተኛ እንደሆነም የጥናቱ ውጤት ያመለክታል። በመጨረሻም በዚህ ጥናት ባልተጨማሩ በሌሎች የግለመር የመማር ዘዴ ንዑሳን ክፍሎች የተለያዩ ጥናት ቢያካሄዱ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለማሳደግ ያለው አስተዋጾ የተሻለ ውጤት እንደሚያመጡ የጥናቱ ውጤት አሳይቷል ።

# ማውጫ


ርዕስ ገጽ

ምስጋና ........ i

አጠቃሎ ........ ii

የሰንጠረዥ ማውጫ ........ vi

ምዕራፍ አንድ

1. መግቢያ ........ vi

1.1. የጥናቱ ዳራ ........ 1

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 4

1.3. የጥናቱ ዓላማ ........ 5

1.4. የጥናቱ ጠቃሜታ ........ 5

1.5 የጥናቱ ወሰን ........ 6

1.6 የጥናቱ ውስንነት ........ 6

1.7 የጥናቱ ቁልፍ ቃላት እና ሀረጋት ብያኔ ........ 7

ምዕራፍ ሁለት ........ 8

2 ክለሳ ድርሳን ........ 8

2.1 ቋንቋን የመማር ዘዴ ........ 8

2.2 ግለመር መማር ዘዴዎች ........ 8

2.3 የግለመር መማር ምንነት ........ 9

2.4 የግለመር መማር ንዑስን ክፍሎች ........ 10

2.5 የግለመር መማር አስፈላጊነት ........ 12

2.6 የግለመር መማር ሂደት ........ 13

2.7 የአንብቦ መረዳት ችሎታ ደረጃ አሳጣጥ ........ 14

2.8 የጥናቱ ንድፈ ሀሳባዊ ትውረት ........ 15

2.9 የግለመር መማር ሞዴሎች ........ 17
2.9.1 የዚመርማን ግለ መር መማር ሞዴል (Zimmerman's Process Oriented Model Of (Self -Regulated Learning ) ........ 17
2.9.2 የፒንቲርችስ አላባ ተኳር (Pintrich's Component Model Of Self-Regulated Learning ) ........ 17
2.9.3 የግለመርመማር ደረጃና ሂደት ሞዴል ........ 18
2.10 ማንበብና አንብቦ መረዳት ችሎታ ........ 18
2.11 የአንብቦ መረዳት ችሎታ አስፈላጊነት ........ 19
2.12 አንብቦ መረዳትን በግለ መምረት ........ 20
2.13 ግለመር የመማር ዘዴ ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያለው ዝምድና ........ 20
2.14 የጥናቱ ፅንስ ሀሳባዊ ማህቀፍ ........ 20
2.15 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት ........ 22
ምዕራፍ ሶስት ........ 24
3. አጠናን ዘዴ ........ 24
3.1 የጥናቱ ንድፍ ........ 24
3.2. የናሙና አመራረጥ ........ 24
3.2.1. የጥናቱ ቦታ አመራረጥ ........ 24
3.2..2..የተማሪዎ ች ናሙና አመራጥ ........ 24
3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ........ 25
3.3.1 የጽሑፍ መጠየቅ ........ 25
3.3.2 የአንብቦ መረዳት ፈተና ........ 26
3.4. የመረጃ መተንተን ........ 27
3.5. የመረጃ አሳባሰብ ሂደት ........ 28
ምዕራፍ አራት ........ 29
4 የመረጃ ትንተናና የውጤት ማብራሪያ ........ 29

4.1 የመረጃ ትንተና ........................................................................................ 29

4.2 የመረጃ ሰጪ ተማሪዎች ዳራ ትንተና ............................................................. 29

ሰንጠረዥ 1 መረጃ ሰጪ ተማሪዎች ዳራ ......................................................... 29

4.3 ተማሪዎች አንብቦ መረዳትን በመማር ሂደት የሚጠቀሟቸው የግለ መር መማር ዘዴዎን መፈተሽ.............................................................................................. 30

4.4 በግለ መር መማር ዘዴና በአንብቦ መረዳት ችሎታ መካከል ያለው ተዛምዶ ፍተሻ31

4.5 ግለመር መማር ዘዴዎች አንብቦ መረዳት ችሎታን የመተንበይ ድርሻ................ 32

4.6 የውጤት ማብራሪያ ....................................................................................... 33

ምዕራፍ አምስት............................................................................................. 38

5.ማጠቃለያና አስተያየት ................................................................................. 38

5.1 ማጠቃለያ ................................................................................................. 38

5.2 አስተያየት ................................................................................................. 39

5.3 መደምደሚያ............................................................................................... 40

ዋቢ ጽሑፎች.................................................................................................... 35

አባሪዎች......................................................................................................... 37

# ሰንጠረዥ ማውጫ

**ርዕስ** **ገፅ**

ሰንጠረዥ 1 መረጃ ሰጪ ተማሪዎች ዳራዊ ሁኔታዎች ........................................30

ሰንጠረዥ 2 ተማሪዎች አንብቦ መረዳትን በመማር ሂደት የሚጠቀሟቸው
የግለመር መማር ዘዴዎች መፋተሽ በቲ -ቴስት ........................................31

ሰንጠረዥ 3 የግለመር የመማር ዘዴና የአንብቦ መረዳት ችሎታ ተዛምዶ
በ ፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ ቀመር (Pearson product of moment ........................32

ሰንጠረዥ 4 ግለመር የመማር ዘዴዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታን የማሳዳግ ድርሻ
የጉልህነት ደረጃ በህብረ ደህረታዊ ትንተና ........................................33

# ምዕራፍ አንድ

## 1.መግቢያ

### 1.1. የጥናቱ ዳራ

ተማሪዎች ትምህርታቸውን በአግባቡ ተከታትለው ጥሩ ውጤት እንዲያመጡ የተለያዩ ችሎታዎችንና ልምዶችን በየጊዜው ማጎልበት ይኖርባቸዋል፡፡ከነዚህም ውስጥ የግለመር መማር ልምድን ማዳበር አንዱና ዋናኛው ነው፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች በግለመር የሚማሩት ትምህርታቸውን ጊዜ ወስደው ማንበብን የሚጠይቅ ነው፡፡ በመሆኑ Farrant(1980,30) እንደገለጽት ተማሪዎች ትምህርታቸውን አዘውትረው የሚያጠኑት በማንበብ ቢሆንም አብዛኞቹ ቀድሞ የግለመር መማርን ስለማያደብሩ ችግር ሲያጋጥማቸው ይታያል፡፡ Grahant (1967,78) በበኩላቸው ጥሩ የግለመር መማር ልምድ ጥሩ ውጤት አስመዝግቦ ትምህርትን ለመማር መሰረታዊ ነገር መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

ይህ ሁኔታ የሚያስረዳው ተማሪዎች በትክክለኛው መንገድ ግለመር የመማር ልምድ ከለጎለበቱ በክፍልም ሆነ በሌላ ቦታዎች የሚጽፏዋቸውን ማስታወሻዎችን አንብበው በመረዳት የሚቀርብላቸውን ንባብ በአግባቡ ለመረዳት እንደማይቸገሩ ነው፡፡ ተስፋዬ (1986፣17-18) አንድ ሰው ቀድሞ የማያውቀውን ሊያውቅ ወይም ቀድሞ ሊሰራው የማይችለውን መስራት ሲችል፣ቀድሞ ሊያደርገው የማይችለውን ሲያደርግ ተማረ እንደሚባልና ይህ የመማር ሂደትም ዝግጅት ያለው እና ዝግጅት የሌለው ተብሎ ሊከፈል ይችላል፡፡፣ዝግጅት ያለው መማር አስተማሪ አካል ያለው ለትምህርትነት የሚቀርበው ይዘት መዋቅር ያለው፣የተወሰነ ጊዜ የተመደበለት ዓላማ ተነድፎለት፣የተወሰነ ቦታ ተሰይሞ የማስተማሪያ መሳሪዎች ተዘጋጅቶለት፣ ብዙ-ጊዜ የአስተሳሰብና የአሰራር ለውጥ የሚመዘንበት ዘዴ ወጥቶለት የሚቀርብ ነው፡፡ ዝግጅት የሌለው የመማር ደግሞ አንድ ሰው የተመደለበት መምህር ሳይገኝ፣ ለሚማረውነገርዝግጅት ሳይኖረው፣በየትኛውም ጊዜና ቦታ በገጠመኝ የሚያገኘው እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ መማር ከመምህር ወይም ከቆይታ ብቻ የምናገኘው ሳይሆን ከዚያ በላይ ሆኖ የሚያካትተው ክሂልን ወይም እውቀትን ማግኘት፣አስተሳሰብን መማር፣ የአመለካከት ለውጥ ማምጣትን፣ ዝንበሌን መልመድን፣ ማህበራዊ እሴትን እንዲሁም የስብዕና ለውጥን ያካተተ በጣም ሰፊ ሀሳብ እንደሆነ Stern (1983,18) ያስረዳሉ፡፡ መማር ሲጠቃላል ያለወቅነውን ጉዳይ በሆነ አጋጣሚ ተቀይሮ ወይም በዝግጅት የምንረዳበትና በመረዳታችንም የሁኔታዎች ለውጥ የምናሳይበት መሆኑን

ከምሁራኑ ሀሳብ መረዳት ይቻላል፡፡

በተጨማሪ ደግሞ ማሪው (1990፣17-18) በተማሪዎች መካከል የስብዕና፣ የማህበራዊ ሁኔታ፣ የፆታ ልዩነት ፣ የዕድሜ ደረጃ ፣የመማር ምርጫ ልዩነት እንዲሰና መምህራን ግን ተማሪዎቻቸውን በአንድ ዓይን ስለሚያያዩቸው ልዩነቱን እንደመይቀባሉ እንዲሁም እነዚህ ልዩነቶች በተማሪዎች በመማር ሂደት ተፅእኖ የሚያሳድሩ ጉዳዮች እንደሆኑ ያመለክታሉ፡፡

Richards& Lockhart (1996,63)እንዲሁም ቋንቋን የመማር ዘዴዎች ተማሪ የሚማሩትን ትምህርት በተለያየ አቅጣጫ በማገነዘብ በግላቸው ፍላጎት በሚሻለቸው መንገድ እንዲማሩ የሚረዳቸው ዘዴዎች ወይም ስልቶች እንደሆኑና በተለይም ተማሪዎች ከመምህራን ጋር ሲገናኙ በማይችሉባቸው ጊዜያት የትኛውንም ትምህርታዊ ጉዳይ በግላቸው እየሰሩ እንዲማሩ የሚረዳቸው መንገዶች በመሆናቸው የቋንቋ ትምህርት ይዘት ተማሪዎች በማይከብድ ሁኔታ እንዲረዱ እንደሚያግዝ ይገልፃሉ፡፡

Pintrich and Degoot (1990,33) ሌሎች ጥናቶችን መነሻ በማድረግ የተለያዩ መማር ዘዴ ሂደቶችን ገልጸዋል፡፡ ይህም የማስታወስ፣የግለመርና አእምሯዊ ዘዴዎች ናቸው፡፡ እንዲሁም በሌላ አቅጣጫ Brown (1994,113) ተማሪዎች ቋንቋን ሲማሩ የሚጠቀሙባቸው የተለያዩ ዓይነት ዘዴዎች እንደሉ ይገልፃሉ፡፡ እነዚህም የመማር ዘዴዎች ፣ማህበራዊ ዘዴዎችና ተግባቦታዊ ዘዴዎች ናቸው፡፡ Eric (2011,5-6) በግለመር የመማር ዘዴ ውስጥ የሚካተቱት ንኡሳን ክፍሎች ግብ ማስቀመጥ፣የመማር ፍላጎትና የመማር ዘዴ እንደሆኑና እነዚህም በተማሪዎች መማር ላይ በጎ ተጽእኖ ያለው መሆናቸውን ያግልጻሉ በተመሳሰይ Ellis (1994,195-196) ከቋንቋ መማር ዘዴ መካከል የግለመር መማር ዘዴዎች ይሁንኝ ተብለው በተማሪ የሚመረጡና የተማሪዎችን መማር ለማፍጠን ወይም ስለ ቋንቋ መረጃውን ለማሰብሰብ፣ለማስታወስ እንዲሁም በተግባር ለመዋል የሚያግዛቸው አቅጣጫ በመሆናቸው ተማሪዎች ሁሌም ዝግጁ እንደሆኑ ከማድረጉም በላይ የመምህራን የማስተማሪያ ዘዴ የተመቻቸ ቢሆንም ባይሆንም ትምህርቱ መመዘኛ ቢኖረውም ባይኖረውም ከመማር ወደኋላ እንደማይሉ ሌላ ድጋፍ ሳያስፈልጋቸው ትምህርቱን በመማርና በማከናውን እንዲረኩ የሚያስቻሏቸው ዘዴዎች እንደሆኑ ይገልጻሉ፡፡

በተጨማሪ Abdurhuman and Nasrha (2012,12) የግለመር የመማር ዘዴ የግልን የመማር ፍላጎት መፈተሸ፣የትምህርት ግብን መቅረፅ፣የመማር ዘዴን የመለየትና የትምህርት ውጤት የመገምገምና ደረጃዎችን ተግባራዊ በማድረግ ተማሪዎች በትምህርት ቤትና ወጭ እንዲገለገሉበት የሚረዳው የግለመር ተነሳሽነት በመሆኑ፤ ከፍተኛ የግለመር የሆኑት ተማሪዎች ዝቅተኛግለመር ከሆኑ ተማሪዎች የበለጠ ውጤታማ መሆንና ለሰፊ ሰዓታት፣ሳፋ የሉትን ጽሑፎችን ማንባብና መረዳት እንደሚችሉ የሳያሉ።

የግለመር የመማር ዘዴ የመጣው በ1980 ዎቹ ሲሆን፣ሰፊ ትኩረት የተሰጠውም በ1990ዎቹ በስነልቦና ትምህርት ከባህሪያዊያን ፍልስፍና ወደ አእምሮዊያን ትምህርት ፍልስፍና ሲሸጋገር መሆኑንና የሀሳቡ የመጀመሪያው አፍላቂ ደግሞ የሥነልቦና ትምህርት ተመራማሪ የሆኑት Zimmreman መሆናቸውን Eric (2011,2) ያስረዳሉ። የግለመር የመማር ዘዴ የበለጠ ትኩረት ማግኘት የጀመረው በቅድመ እውቀት ግንባታዊያን ንድፈ ሀሳብ (constructivist theory ) እና በማህበራ አእምሯታዊያን ንድፈ ሀሳብ (Social cognitive theory) እንደሆነ Bandura, (2001,14) ገልጸዋል እንደ Block (1997) አገላለፅ በ1990ዎቹ አገልግሎት ላይ የዋለው የማህበራዊ እውቀት ግንባታ ንድፍ ሀሳብ ዕይታ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ዕድገት የማያቋርጥ ሂደት መሆኑን የሚያሳይ ሲሆን ከውልደት ጀምሮ በተለያየ መጠን እያደገ በመሄድ እስከ ሕይወት መጨረሻ እንደሚዘልቅና ተማሪዎች አደዲስ የመማር ዘዴዎችን የሚለምዱት ባላቸው ግለሰባዊ ልምድ መሆኑን እና የግለመር የመማር ዘዴንና የአንብቦ መረዳት ተግባራትን የሚወጡት ደግሞ ከቤተሰቦቻቸው፣ ከማህበረሰቡ፣ ባህላዊና ማህበራዊ አካባቢዎች በመማር እንደሆነ ያብራራሉ። እንደ ግንባታዊያን ንድፍ ሀሳብ ተማሪዎቹ የሚያነቡትን ነገር የሚተረጉሙት ወይም የሚገነዘቡት አስቀድሞ ካለቸው እውቀት ጋር በማዛመድ ነው። እያንዳንዱ ተማሪ የቀደመ ልምዱን ከአዲሱ እውቀት ጋር በማዋሀድና በማስማማት እውቀት ይገነባል፤ በመሆኑም ንባብ አእምሮዊ ሂደት ስለሆነ የተማሪውን ግለመሪነት እንደሚፈልግ (Alijuaid and thallab, 2015,45) ይገልፃሉ።

Zimmerman (2002,66-67) የግለመር የመማር ዘዴን ለማዳበር አራት ሂዳቶችን በቅደመ ተከተል መተግባር እንደለበት ይገልጻሉ። ይህም የራስ ምልከታ ማድረግ፣ግብ መጣል፣የእውቀት ትግበራናየውጤት ቁጥጥር ናቸው። በዚህ መንገድ ተማሪዎች የግል ብቃት በመፈተሽ እየገመገሙ ለራሳቸው ውሳኔ ይሰጣሉ። በግለመር የመማር ሂደት ጊዜ

የተማሪዎች ተግባርም የሚያጠኑትን ይዘት ማረጋገጥ፣ለመማር የሚያስቸግራቸውን መገምገም፣መሻሻላቸውን መከታተል፣ የመማር ውጤታቸውን መፈተሽ እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡ እንዲሁም ከቀረቡት ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው ግለመር መማር ዘዴዎች ትልቅ ጠቃሚታ ያላቸውና በመማር ውጤት ላይበጎ ተፅእኖ የሚኖር ከመሆናቸውም በላይ ትምህርት እስከ ሕይወት መብቂያ የሚዛልቅ በመሆኑ ለተግባር ውጤታማነት ያጎለ ድጋፍ አለው፡፡ በመሆኑም ግለመር መማር ዘዴ ተጠቃሚ ለመሆን ጥናት ማድረግ ተገቢ ይሆናል፡፡ ይህ ምርምርም የግለመር የመማር ዘዴን በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተማሪዎች አንብቦ ከመረዳት ችሎታ ጋር ያለውን ተዛምዶ አሳይቷል፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

አጥኚው በጃርሶ ኦንጀጆ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ባቆየባቸው ጊዜያት በዘጠነኛ ክፍል የሚማሩ ተማሪዎች በንባብ ጊዜ ተሳትፎ ዝቅተኛ መሆን፣የሚቀርበላቸውን ንባብ ለማንባብ ፍላጎትና መነቃቀትና አለመኖርና ከዚህ በመነሳት የአንብቦ የመረዳት ጥያቄ በሚሰጥበት ወቅት፣አንደንድ ተማሪዎች በአንብቦ መረዳት ልዩ ትኩረት ሲሰጡ አንደንዶቹ ደግሞ ትኩረት እንደማያሳዩ ተይቷል፡፡ እንዲሁም ተማሪዎች ግለመር አንባቢ ለመሆን ስሜታቸውን ፣የመማር ግባቸውን፣ግንዛቤያቸውንና መሰልቸታቸውን ለመቆጣጠር አስፈላጊ የሆኑ ክሂሎች ለማሳደግ ያለው ተነሳሽነት አነስተኛ እንደሆነ ተይቷል፡፡ ከዚህ በመነሳት የተወሰኑ የተማሪዎች የተሻለ ውጤት ሲያሳዩ የተወሰኑቱ ደግሞ ዝቅተኛ ውጤት ማስመዝገባቸውን ተገንዘቧል፡፡

እንዲሁም ከቋንቋ ትምህርት ዓላማዎች ውስጥ ቀዳምዉ የተማሪዎችን የአንብቦ ከመረዳት ችሎታ ማሻሸሉ አንዱ ተግባር ነው፡፡ እንዲሁም ተማሪዎች አንድን ምንባብ በትኩረት አንብቦው መረዳት ችሎታ በአብዛኛው ዘንድ እንደሌላቸው የተለያዩ ጥናቶች ተካሄደዋል፡፡ cole(1996,23) እንደሚገልጹት በርካታ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የዳበረ አንብቦ የመረዳት ልምድ የላቸውም፡፡የሚያነቡትን ምንባብ በጥልቀት እንደማይመለከቱት ይገልጻል፡፡ እንዲሁም Conley (1992,15) የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ በሚማሩት ትምህርት ላይ እንዲሁም በትምህርት ቤት ቆይታቸው ተፈላጊ ቦታ ወይም ደረጃ ሳይደርስ ይቀራል፡፡ እነዚህም ችግሮች የሚጠቀሰው መምህራን አንብቦ የመረዳትን ችሎታ ሲያስተምሩ ግለመር የመማር ዘዴዎች በተገቢው ሁኔታ አለማለማመዳቸውን ይገልፃል፡፡

በመሆኑም ይህ ጥናት ከላይ የቀረቡትን ችግሮች እንደ ምክንያት በመጠቀም በጃርሶ ኦንጀጆ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት በ9ኛ ክፍል በተማሪዎች የግለመር የመማር ዘዴና የአንብቦ

መረዳትችሎታለመፈተሽ ተነሳስቷዋል፡፡ በዚህ መነሻ ጥናቱ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ጥረት ተደርጓል፡፡

1. የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች አንብቦ መረዳትን በሚማሩበት ጊዜ የሚጠቀሟቸው የግለመር የመማር ዘዴዎች የትኞዎቹ ናቸው?
2. የግለመር የመማር ዘዴዎችና አንብቦ ከመረዳት ችሎታ መካከል ያለው ተዛምዶ ምን ይመስላል ?
3. የግለመር የመማር ዘዴ አንብቦ የመረዳት ችሎታን የማሳደግ ድርሻው ምን ያህል ነው ?

## 1.3. የጥናቱ ዓላማ

ይህ ጥናት ዋና ዓላማ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውስጥ በተማሪዎች አንብቦ መረዳት ችሎታን በግለመር የመማር ዘዴ መካከል ያለውን ተዛምዶ መፈተሽ ነው፡፡ በዚህ ዋና ዓለማ ስርም የሚከተሉት ንዑሳን ዓላማዎች በጥናቱ ተካተዋል፡፡

1. የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች አንብቦ መረዳትን በመማር ሂደት የሚጠቅሟቸውን ግለመር የመማር ዘዴን መፈተሸ፣
2. በግለመር መማር ዘዴና አንብቦ መረዳት ችሎታ መካከል ያለውን ተዛምዶ መመርመርና፤
3. የግለመር የመማር ዘዴ የአንብቦ መረዳት ችሎታ የማሳደግ ድርሻው ምን ያህል እንደሆነ መፈተሽ ናቸው፡፡

## 1.4. የጥናቱ ጠቃሜታ

ይህ ምርምር በዋናነት ግለመር የመማር ዘዴ አጠቃቀም ከተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያለውን ዝምድና በማሳየት መረጃ ሊሰጥ ይችላል፡፡ በተጨማሪም የሚከተሉት ጠቃሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታመናል፡፡

1. ተማሪዎች ትምህርታቸውን በራሳቸው ግብና ተነሳሽነት መማር ያለውን ፋይዳ ሊጠቁም ይቻላል፡፡
2. ግለመር የመማር ዘዴ ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያለውን ዝምድና በማሳየት መምህራን ለተማሪዎች የሚሰጡትን የመማር ማስተማር ድጋፍ ሊያጠናክር ይችላል፡፡ እንዲሁም ውጤታማ ተማሪዎች የሚጠቀሟቸውን የመማር ዘዴዎች በመለየት የአንብቦ መረዳት ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች ለማጠናከር የዘዴው

ስልጠና ለመስጠት ሊያግዝ ይችላል፡፡

3. የቋንቋ መምህራን የተማሪዎቻቸውን የግለመር የመማር ዘዴ አጠቃቀም በመለየት የትምህርት አቀራረባቸውን፣ የማስተማሪያ መሳሪያዎቻቸውንና የዕለት እቅደቻቸውን ከግለመር የመማር ዘዴ አጠቃቀም አንፃር እንዲያዘጋጁ ሊያግዝ ይችላል፡፡
4. በግለመር መማር ዘዴና በአንብቦ መረዳት ችሎታ ዙሪያ በስፋት ለማጥናት ለሚፈልጉ ባለሙያዎች የተወሰነ መረጃ ሊሰጥ ይችላል፡፡

## 1.5. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በተማሪዎች ግለመር መማር ዘዴ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያለውን ተዛምዶ በመፈተሽ ላይ ብቻ የተወሰነ ነው፡፡ አጥኚው ካለበት የጊዜና የገንዘብ ውስንነት የተነሳ የሚካሄዳው በሀዲያ ዞን በምዕራብ ባዳዋቾ ወረዳ በጃርሶ ኦንጆጆ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት  በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ብቻ ነው፡፡ ተሳታፊ ተማሪዎች የተመረጡት በ2015 ዓ.ም በጃርሶ ኦንጆጆ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት  በመማር ላይ ከሚገኙት ከ9ኛ-12ኛ ክፍል ተማሪዎች ውስጥ በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተወሰነ ነው፡፡
አጥኚው ከለባት የጊዜ የገንዛብ ውስንነት የተነሳ የሚካሄደው በሀዲያ ዞን ምዕራብ ባዳዋቾ ወረዳ በጃርሶ ኦንጆንጆ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 9ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ብቻ ነው፡፡ ተሳታፊ ተማሪዎች የተመረጡት በ2015 ዓ.ም ያሉ በመሆኑ ነው፡፡
ጥናቱ የሚመለከታቸው ጉዳዮች በግለመር የመማር ዘዴዎች ስር የሚካታቱን ንዑሳን ዘዴዎች ማለትም ግብ ማስቀመጥ፣የመማር ፍላጎትና  የመማር ዘዴዎች ይህም ግለመር የመማር ዘዴና የአንብቦ መረዳት ችሎታ ያላቸው ዝምድና፣ ስለ ግለመር መማር ዘዴዎች ላይ የተወሰነ ነው፡፡

## 1.6 የጥናቱ ውስንነት

የትኛውም የጥናትና የምርምር ተግባረ የራሱ የሆነ ክፍተቶች ወይም ጉድለቶች ሊያገጥሙት ይችላል ፡፡ይህ ጥናታዊ ፅሁፍም በሀዲያ ዞን በምዕራብ ባዳዋቾ ወረዳ ጃርሶ ኦንጆጆ 2ኛ ደረጃ ትም/ቤት በ9ኛ ክፍል ላይ ብቻ ትኩረት ያደረገ በመሆኑ ውስንነት ተይዟዋል፡፡ሌላው በግለመር መማር ዘዴና አንብቦ ከመረዳት ችሎታ መካከል ያለውን ተዛምዶ መፋተሽ ላይ ብቻ በመድረጉ ውስንነት  ሲኖረው  እንዲሁም  ለጥናቱ  አስፈላጊ ግብአቶችን ለማሟላት የገንዘብ እጥረት እንዲሁም  እያንዳንዱ ተላውጦ እርስ በርስ ያለውን ግንኙነትና ነፃ ተለውጦን ጥገኛ ተለወጦን የማሳደግ ድርሻውን ማየት አስፈላጊ በመሆኑ ባርካታ

ናሙናዎችን ወስዶ መስረት አለመቻሉ አንዱ የጥናቱ ውስንነት ነው፡፡በተጨመሪም ጥናት በሚዘጋጅበት ወቅት በግለመር መማር ዘዴ ዙሪያ የታተሙ ድርሳናት በበቂ ሁኔታ ያለማገኛት ውስንነት ተይቷል፡፡

## 1.7 የጥናቱ ቁልፍ ቃላት እና ፅንሳ ሀሳቦች ብያኔ

- ✓ **ግለመር የመማር ዘዴ፡-**ይሁነኝ ተብለው በተማሪዎች የሚመረጡና ተማሪዎች መማራቸውን ለማፋጠን የሚያግዙ ስልቶች ናቸው፡፡
- ✓ **አንብቦ መረዳት ችሎታ፡-**አንድን ምንባብ መረዳት፣ምንባቡ የያዘውን አስፈላጊ መረጃ በሚቻለው መጠን መገንዘብ፣የምንባቡን አውዳዊና ከአውድ ውጭ የሆኑ ፍችዎችን ሁሉ መረዳት ያጣቀልላል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## 2 ክለሳ ድርሳን

### 2.1. ቋንቋን የመማር ዘዴ

ቋንቋን የመማር ዘዴዎች ተማሪዎች የሚማሩትን ትምህርት በተለያየ መንገድ በማገነዘብ በግለቸው ፍላጎት በሚሻለው መንገድ እንዲሄዱ ወይም እንዲማሩ የሚረዳቸው ዘዴዎች ሲሆኑ በተለይም ተማሪዎች ደጋፊ ሰዎችን ሊያገኟቸው በማይችሉባቸው ጊዜያት ማንኛውንም ትምህርታዊ ተግባር በግላቸው እየሰሩ እንዲማሩ የሚረዷቸው እና ተማሪዎች በመማር ሂደት ውስጥ ተግበራዊ የሚያደርጓቸው ዘዴዎች እንደሆኑ (Richards and Lockhart, 1996,63) ያብራራል።

እንዲሁም የመማር ዘዴዎች ተማሪው የትምህቱን አቅጣጫ የተሳካ ለማድረግ ስነ ልሳናዊና ይዘታዊ መረጃዎችን ለማገነዘብ የሚያደርጉ አቅጣጫዎችና ዘዴዎች ሲሆኑ ግለሰቦች ለመረዳት፣መረጃ ለማሰበሰብ፣ጥሩ የሆነውን ነገር ለማግኘት፣እንዲሁም መማርን ለመፈተሽና ለመገምገም ወይም የተለያዩ ድርጊት ለማከናወን የሚረዳቸው አስተሳሰቦች፣ ውሳኔዎችና ዘዴዎች እንዲሆኑ እና በመማር ጊዜ ውስጥ የአጭር ጊዜ የትውስታ ችሎታ ውስንነት ለማሻሸልና መረጃን ከአጭር ጊዜ ትውስታ ወደ ረጅም ጊዜ ትውስታ አሸጋግሮ ለመጠቀም የሚያስችሉ፣ ተማሪዎች መረጃን በጥሩ ሁኔታ ውጤታማ በሆነ አቅጣጫ ለማሰብሰብ እንዲሁም ለመግለጽ የሚያስችለው ሁኔታዎች መሆናቸውን Chamot, (1989,13-24) ይገልጻሉ።

### 2.2. ግለመር መማር ዘዴዎች

ግለመር የመማር ዘዴ ተማሪዎች የግል ግባቸውን እንዲጥሉ፣ የግባቸውን አፈፃፀም እንዲለዩ የሚያስችሏቸው፣ ተማሪዎች እራሳቸውን እና ድርጊታቸውን እንድቆጣጠር የሚያስችሏቸው እንደሆኑ እና ተማሪዎች የቋንቋ ትምህርት ሲማሩ የትምህርቱን የመማር ሂደት የሚያቀለጥፉ ስለሚማሩበት የቋንቋ ትምህርት ይዘት አይራሴ የሚያደርጉ ተማሪዎች በቀላሉ ይዘቶችን ትምህርቱን አስተውሶ እንዲጠቀሙ የሚያደርጉ ዘዴዎች ሲሆኑ ተማሪዎች የመምህሩ የማስተማር ዘዴ ቢመቻቸውም ባይመቻቸውም ትምህርቱ ፈተና ቢኖረውም ባይኖረውም ከመማር ምንም አይነት ግፊት ሳያስፈልጋቸው ትምህርቱን በመማርና ተግባራቱን በማከናወን እንድረኩ የሚያደርጉ ዘዴዎች መሆናቸውን (Ellis,

1994) ያስረዳሉ።

Abdurhuman& Nasrha (2012,12) ግለመር የመማር ዘዴ የግልን የመማር ግንዛቤ መፈተሽ፣የትምህርት ግብን መቅረጽ፣የመማር ዘዴን የመምረጥ፣የትምህርቱን ውጤት መገምገምን የሚመለከቱና ተማሪዎች በትምህርት ቤትና ከትምህርት ቤት ወጭ ሊያከናውኗቸው የሚችሉባቸው የማንበብ ከአውዱ አንጻር ሐሳቡን በትክክል መረዳት እንዲችሉ ተጽዕኖ የሚያሳድር መንገዶች ሲሆን ከፍተኛ የግለመር የሆኑ ተማሪዎች ዝቅተኛ ግለመር የሆኑ ተማሪዎች የተሸለ ውጤታማ እንደሆኑ እንዲሁም ለረጅም ሰዓታት፣ በርካታ ጽሑፎችን ማንበብና መረዳት እንደሚችሉ ያጠኑትን ጥናት መሠረት መነሻ በማድረግ ይገልፃሉ።

Cole (1996,23) እና Conely (1992,15) በደረጉት ጥናት ያገኙት ውጤት መምህራን አንብቦ የመረዳትን በክፍል ሲያስተምሩ የግለመር መማር ዘዴዎች ባለመተግባራቸው በርካታ በ2ኛ ደረጃ ያሉት ተማሪዎች የዳበረ የአንብቦ መረዳት ልምድ እንደሌላቸውና የሚያነቡትን ምንባብ በትኩረት እንደማይመለከቱ በመግለፅ ተማሪዎቹ ትምህርታቸውን ሲያጠነቅቁ የአንብቦ መረዳት ችሎታቸው ጥሩ ደረጃ ሳይዳርስ እንደሚቀር ይገልፃሉ።

## 2.3 የግለመር መማር ምንነት

የግለመር መማር ከግል የሚመነጭ ግለሰባዊ ግብና ዕቅድ የያዘ ሀሳብ፣ድርጊት ሲሆን ተማሪዎች ያቀዱትን የሚተገብሩበት፣አፈጻጸመቸውን የሚገመግሙበት፣የግል ብቃታቸውን በመለየትና በመፈተሽ ለግለቸው ውሳኔ የሚሰጡበት ነው። ተማሪዎች በተግባር የሚያጠኑትን ይዘት እያረጋገጡ፣ለመማር የሚያስቸግራቸውን በመገምገምና በመከተተል የመማር ውጤታቸውን የመቆጣጠር ሂደት ነው።

በዋናነት የግለመር መማርን በትምህርት እንቅስቀሴ ውስጥ "የግለሰቦች ተሳትፎ በመማር ውስጥ ያለው ጠቃሜታ" በሚል ርዕስ በ1963 Gardner የተባለ ምሁር እንዳስተዋወቀው (zimmerman. 1990, 3) ያስረዳል። ኋላም የGardner አማለካከት የትምህርት ስርዓት ሙሉ በሙሉ ወደ ግለሰቦች በመለወጡ ንድፈ ሀሳቡ የይሁንታ ችግር እንደገጠመው (Mohammed & salmani 2012,1) ያጠኑትን ጥናት መሠረት በማድረግ ይገልፃሉ።

በ1990ዎቹ Zimmerman የተባለ ምሁር" በምልካታ መማር/Observational Learning) የሚል አዲስ ሀሳብ ያመነጨ ቢሆንም በ1974 ይህንን ሀሳብ የበለጠ በማሳደግ"የግለመር መማር" (Self Regulated Learning)የሚለውን የሰተዋወቀ ሲሆን ንድፈ ሀሳቡም በትምህርት ባለሙያዎች፣በተለያዩ የምርምር ተቋማት ከፍተኛ የሆነ ተቀባይነት እንዳለው

(Mohammed & Salmani, 2012፣1)ያስረዳሉ።

እንዲሁም Eric(2011፣2) የግለመር የመማር ዘዴ የመጣው በ1980ዎቹ ሲሆን ትልቅ ትኩረት የገኘውም በ1990ዎቹ የስነ-ልቦና ትምህርት ከባህሪያዊያን ፍልስፍና ወደ አእምሮዊያን የትምህርት ፍልስፍና ሲሸጋገር እንደነበረ በማሳየት የእውቀቱ ቀዳሚ አመንጭም የስነልቦና ትምህርት ተመረማሪ የሆኑት Zimmerman እንደሆነ ይገልፃል።

## 2.4. የግለመር መማር ንዑስን ክፍሎች

Brown (1994,113-114) ተማሪዎች ቋንቋ ሲማሩ የሚጠቀሙባቸው ሶስት ዓይነት ዘዴዎች እንደሉ ይገልፃሉ። ይህም የመማር ዘዴ፣ተግባቦታዊ ዘዴና ማህበራዊ ዘዴዎች ስገልጽ Eric (2011,5-6) በተጨማሪም በግለመር መማር ዘዴ ስር የሚኖሩ ንዑሳን ክፍሎች የመማር ፍላጎት፣ግብ ማስቀመጥና የመማር ዘዴዎች እንደሆኑ ይገልፃሉ። እነዚህም ፡-

### ሀ. ግብ ማስቀመጥ

በቋንቋ ማስተማሪያ አቅጣጫ ከተግባቦታዊ፣ከስሜታዊ፣ከአካላዊ የትምህርት ውጤቶች በተገኘው ቀጣይ ሊደረስበት የታለመ ሀሳብን የሚያሳይ ነው። እንዲሁም ግብ ተማሪው የሚፈለገውን ደረጃ ውጤት የሚያሳይ ሲሆን ተማሪዎች የትኛውንም ሥራ ከመከናወነቸው በፊት ግባቸውን እንድያሰቀምጡ ማድረግ፣ መነሳሳት ለቀጠዩ የመማር ዘዴዎችን ማከናውን ስጀምሩ ጊዜያቸውንና አቅማቸውን በመጠቀም ውጤታማ እንዲሆኑ ያግዛቸዋል።እንደ Eric(2011,6)ግብ ተማሪዎች ከትምህርቱ በኋላ የሚያገኙት ውጤት ተማሪዎች በግለቸው የሚማሩ እንዲሆኑ አቅጣጫ በመክፈት ሊያግዟቸው እንደሚችል፤ እንዲሁም ተማሪዎች ዝርዝር አላማቸውን እንዲያቅዱ በመገዝ የሚጥሉት ግብም ትክክለኛ፣ውስን፣ዝርዝር ክንዋኔዎች የሚያሳይ፣የሚለካና በጊዜ የተወሰነ መሆኑን፣ተማሪዎች የሚጥሉት ግብም የሚያነቡትን ጽሁፍ በቀላሉ እንዲረዱ እንደሚያደርገቸው በማስገንዘብና በማገዝ መምህራን በቅዲሚያ ተማሪዎች የስቀመጡትን ግብ መገምገምና ችግራቸውን እንዲፅፉ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፣ከተወሳኑ ጊዜ በኋላም የነደፉትን ግብ እንደገና እንዲመለከቱና ግልፅ ያልሆነውን እንዲሰርዙ መጠቆም፣ከዚያም ግባቸውን ከመማር ማሰተማር ሂደት ጋር በማዛማድ የጊዜ ሰሌዳቸውን እንዲፈትሹና እንዲሰፍሩ ማድረግ፣ግባቸውን ለማሳከት ሊገጥሟቸው የሚችሉ ችግሮችን በመለየት የመፍትሔ ዘዴዎችን እንዲያቅዱ ማስረዳት፣ተማሪዎች ከግባቸው አንፃር የትምህርት ውጤታቸውን እንዲተነብዩ፣ እንዲገምቱ ማድረግ አቅጣጫ መመልከትና በመጨረሻም ተማሪዎች ከግባቸው እንዲደርሱ ማበረታተትና ለድክማቶቻቸው ሁሉ አዎንታዊ ግብረ መልስ በመስጠት መደጋፍ

እንደሚያስፈልግና ተማሪ የተለያየ የመማር ግብ፣ችሎታና ስኬት ስላለው መምህራንም ግባቸውን ያሳኩ ተማሪዎች የበለጠ ከበድ ያሉ ግቦችን እንድጥሉ ማገዝና ከግባቸው ያልደረሱትን ደግሞ ግባቸውን እንደገና እንድፈትሹና እንድያሳኩ ከፍተኛ ጥረት በመድረግ ዘዴዎቻቸውን እንዲያስተካክሉ ማበረታተት እንዲሚጠበቅባቸው ያስረደሉ።

**ለ. የመማር ፍላጎት**

ፍላጎት ንቁ በሆነ አእዕምሮ ወይም በንቃተ ህሊና አንድን ተግባር ለማከናውን የሚደረግ ጥረትን የሚደጋገፍ አእዕምሮታዊና ስሜታዊ መነቃቀት ሲሆን አንድን ቋንቋ ለመማር የሚኖረን ቀና አስተሳሰብ ተከትሎ የሚፋጠር ውስጣዊ የሆነ ፍላጎትና መነሳሳት መሆኑን፣ ፍላጎት የተማሪዎችን ተነሳሽነት፣ስሜት፣የሚያሳይ፣ከውስጣዊና ውጫዊ ግፊት የሚፈጠር መልካም አሰተሳሰብ፣ በጎ ምላሽን፣የተሸለውን ውጤትን የሚያስገኝ አንድ ተግባር እንዲፈጸም የሚያነሳሳ ተማሪዎች ወደተሻለው መንገድ እንዲጓዙ የሚያደርግ ጊዜያዊና ዘላቂነት ያለው የማነቃቅያ መንገድ መሆኑን (Harmar, 2001,52) ያስረዳሉ።

**ሐ. የመማር ዘዴዎች**

የመማር ዘዴዎች ተማሪው የትምህርቱን አቅጣጫ የተሳካ ለማድረግ የቋንቋ ስነ-ልሳናዊና ይዘታዊ መረጃዎችን ለማስታዎስ የሚረዱ አቅራረቦችና ቴክኒኮች ሲሆን ግለሰቦች አንድን ሀሳብ ለመረዳት፣መረጃ በመገኘት፣የተሻለ ነገር ለመቆጣጠርና ለመፈተሽ ወይም የተወሳነ ተግባር ለማከናወን የሚጠቀሙባቸው አስተሳሰቦች፣ዘዴዎች  እንዲሁም በመማር ሂደት የቅርብ ጊዜ ትውስታ ወደ ቀጣይነት ለመሸጋጋርና ለመጠቀም ተማሪዎች የበለጠ ውጤታማ እንደሆኑ ይረዳችኋል።

አእምሮታዊ የመማር ዘዴ፦ እንደ Stern (1983,469) ገለፃ ተማሪው ለትምህርት በቀረበው ቋንቋ ላይ እንዲያተኩርና ይህንንም በአግባቡ እንዲረዳ የሚያደርገው እና ተማሪው በቋንቋ መዋቅር ላይ አእምሮአዊ ቁጥጥር በማድረግ በቀጥታ በቋንቋው ወደ መጠቀም እንዲያመራ የሚያስችለው ዘዴ ሲሆን ተማሪዎች የቀረበውን ፅሁፍ በግለቸው ለማፈ፣ተግባራትን ለመፈጸም እንዲሁም የሚያገጥሟቸውን ችግሮች ለመቀላል የሚረዷቸው ዘዴ ሲሆን የንባብ ቅደምተከተልን በማዘጋጀት ፅሁፉን ለማከላስ፣ለመስተዋስ፣ለመተንተን  ተስቦ የሚከናውን ተግባር በመሆኑ ተማሪዎች አዳዲስ እውቀቶችን ቀደም ሲል ከሚያውቋቸው ጋር ለማዛመድ፣ ለመተንተንና፣ በዓይነት ለማደራጀት እንደሚገለገሉበት ይገልፃሉ።

ማህበረሰባዊ ዘዴ፦ተማሪው ከክፍል ጓደኞቹ ወይም ከሌሎች ሰዎች ጋር ማህባረዊ ግንኙነት በመድርግ እንዲማሩ የሚያደርግ ዘዴ ተማሪዎች ከክፍል ተማሪዎቻቸው ጋር እያሆኑ ግልፅ ያልሆነውን ወይም እርግጠኛ ያልሆኑበትን ትምህርታዊ ተግባረትን ሌሎች ሰዎችን

በመጠያቅና እንዲማሩ የሚያደርጋቸው ዘዴ ነው፡፡ተማሪዎች በቋንቋው የመናገር ችሎታ ካላቸው ሰዎች በመሆን መልካሞ ግንኙነትና ዘዴን በማዳበር፣ከእኩያዎቻቸው ጋር በመተባበር እንዲሁም በመናጋገር የሚማሩበት መሆኑን (Oxford,1990, 55)ይገልጻሉ፡፡

.የማካከስ ዘዴ፦ተማሪዎች በቋንቋው እውቀታቸውን ሲጠቀሙ የሚኖረቸውን የመረጃ ውስንነት ለማሻሻልና ክፍተቱንለመሸፈን እንደሚገለገሉባቸው እና ተማሪዎች የገጠማቸውን የእውቀት ማነስ ለማስተካከል የሚያስችል በተለይም በዚቅተኛና በመካከለኛ ደረጃ ለሆኑ የቋንቋ ተማሪዎች በጣም ተገቢ እንደሆነ (Zimmerman,2008,87) ይገልጻሉ፡፡ Ellis (1994,165) በቋንቋ መማር ሂደት ተማሪዎች የቋንቋ እውቀት እጥረት በሚያገጥማቸው ወቅት እጥረቱን ለማስወገድ የማካከስ መማር ዘዴ አጠቃቀም ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው ያብራራሉ፡፡

ስሜት መቆጣጠር ዘዴ፦ከተማሪው ስሜት፣አስተሳሰብና ተነሳሽነት ጋር የተያየዙ ተማሪው በትምህርቱ ሂደት የሚኖረውን የፍርሃትና የመረበሽ ስሜት እንዲሁም አሉታዊ አስተሳሰብ ለመቋቋም የሚጠቀማቸው እና ተማሪዎች በመማሪያ ክፍልም ሆነ ውጭ ከቋንቋ ተናጋሪዎች ጋር በሚያደረጉት ግንኙነት የቋንቋው ዕውቀት ዚቅተኛ መሆኑን ከህብረተሰቡ ጋር ባለው መግባበት በቅርበት በመማር ፍላጎትና በንቁ ሁኔታ የመሳተፍ ስሜት ላይ በተወሰነ ደረጃ ጫናና የስሜት መረበሽ መኖረቸው የማይቀር በመሆኑ የቋንቋ ተማሪዎች በውስጣቸው የተፈጠረውን የመረበሽ ስሜት ለመቋቋም የሚጥሩበት እንዲሁም ተማሪዎቹ ራሳቸውን እንደ አንድ የቋንቋ የተማሪ በመሆን ለተተኳሪ ቋንቋ፣ባህሉና ህብረተሰቡ መልካም አስተሳሰብ የሚፈጥሩበት መንገድ ይህን ባህርያት አስቀድሞ በመለየት የሚከናወኑበት ዘዴ ስሜትን የመግታት ዘዴ እንደሆነ (Oxford,1990,53)ይገልጻሉ፡፡

## 2.5 የግለመር መማር አስፈላጊነት

Pintrich (1995, 7-9) ግለመር መማር ሰፊ ጠቃሜታዎች እንዳሉት ይገልፃሉ፡፡ እነዚህም ጠቀሜታዎች ተማሪዎች ሲማሩ ረስአገዝ እንዲሆኑ ማስቻል ማለትም ተማሪዎች የሚማሩትን ትምህርታዊ የሆኑ ተግባራት በግላቸው እይታ እያዩ፣እየለዩ፣እየገመገሙ፣ እንዲማሩ ያግዛቸዋል፡፡

በተጨማሪም በተማሪው መካከል የዕድሜ፣የፆታ፣የችሎታና ዕውቀት መነስና መዳግ እንዲሁም የመማር ፍላጎት ልዩነት ተፅእኖ ሳይኖሩባቸው እንዲማሩ ያግዛቸዋል፣ግለመር መማር በግል ቁጥጥር ውስጥ የሚሆን በመሆኑ ተማሪው የግሉን አመለካከት፣ ማነሳሳታቸውን፣ መልካም ተግባሮቻቸውን፣ እንዲሁም አስተሳሰበቸውን እንዲፈትሹ

የሚያደርጋቸው በመሆኑ ትምህርታቸውን የመማር ትኩረት እንዲያሻሽሉ ይረዳቸዋል፡፡ Abas and et'al(2016)"ራስመር የመማር ብልሀቶች የአንብቦ መረዳት ችሎታን የመተንበይ ድርሻ"በሚል ጥናት የካሄዱ ሲሆኑ የጥናቱ አላማም ራስመር የመማር ዘዴዎችን በአንብቦ መረዳት መካከል ያለውን ግንኙነት መመርመር ነው፡፡ የጥናቱ ውጤትም ራስመር የመማር ዘዴዎች  የአንብቦ መረዳት ችሎታን እንደሚተናብዩ አሳይቷል፡፡ከዚሁ ጋር ተያይዘው Eric(2011)የራስመር የመማር ብቃትን ለመዳበር ያለው ፋይዳ "በሚል ርዕስ ጥናት ያካሄዱ ሲሆን የመማር ፍላጎት፣ግብ ማስቀመጥ፣ድርጊት ቁጥጥር እንዲሁም የመማር ዘዴዎች የተማሪዎችን የመማር ብቃት ለማሻሽል ከፍተኛ የሆነ ሚና እንዳሚጨወቱ የጥናቱ ውጤት አሳይቷል፡፡ እንዲሁም Najva(2015)"ራስመር መማር ብልህቱን ማስተማር በተማሪዎች አንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ያለው  ተጽዕኖ"በሚል ርዕስ ጥናት አካሄዷዋል፡፡ የጥናቱ ውጤትም ራስመር የመማር ብህልቶችን ማስተማር በተማሪዎች አንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ጉልህ የሆነ ተፅእኖ እንዳላቸው የጥናቱ ውጤት ያሳያል፡፡ በመጨረሻም ከእነዚህ ተመራማሪዎች ሀሳብ የምንገነዘበው የግለመር መማር ለአንብቦ መረዳት ችሎታ መጎልበት ከፍተኛ ሚና  እንዳላው መረዳት ይቻላል፡፡

ተማሪዎች ለመማር ኃላፊነት ለመውሰድና መማራቸውን በግላቸው እየተቆጣጠሩ ለመሄድ አቅም እንደለው እንዲሰማቸው ይረዳቸዋል፣ ግለመር መማር ለተማሪው የሚስማማ ስለሆነ ተማሪዎች ጊዜያቸውን በሥርዓት በመተግባር ትምህርት ቤት በሚሰሩ ሥራዎችና ለመማር ማስተማር ከሚዘጋጁ ፕሮግራሞች ጋር እንዲጣጣም በማድረግ ትምህርታቸውን እንዲከታተሉና እንዲያጠኑ የተሻለ አስተዋጾ አለው፡፡ ግለመር መማር ተማሪዎች ስለአመለካከት ስለተነሳሽነት እና አስተሳሰብ ችሎታቸው ግንዛቤ እንዲፈጥርላቸው በማድረግ ድክመታቸውንና ጥንካሬያቸውን እንዲለዩ የሚያደርግ ስለሆነ የመማር ውጤታቸው ላይ በጎ ለውጥ እንዲያሳዩ ይረዳቸዋል፣ግለመር መማር ተማሪው በሚማሩት ትምህርት ላይ እንዲያትኩሩ በማድረግ በሚማሩት ትምህርት ላይ ብቃት እንዲኖር እንደሚያደርገቸው ያመለክታሉ፡፡

## 2.6 የግለመር መማር ሂደት

በግለመር የመማር ችሎታ ማዳበር ደረጀ በደረጃ የሚከናወን ሂደት ነው፡፡ በእያንዳንዱ የመማር ሂደት  ተማሪዎች ንቁ ተሳትፎ ይህ ሂደትዊ ድግግሞሽ የግለመር መማር ችሎታ በአውድ ላይ ተመስርቶ የተማሪውን ንቁ ተሳትፎ እንደምጠይቅ Zimmerman (2002) ይገልጻል፡፡ እንዲሁም ግለመር የመማር ችሎታ አውዳዊ ባህር ስላለው እርስ በርስ

መስተጋብር በተሻለ የሚዳብር ነው ግለመር መማር የተማሪዎችን ውጤታማነት ከሚወስኑት ቁልፍ ነገሮች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ምንም እንኳ ግለመር የመማር ብቃትን በግል ማዳበር ቢቻልም ይህ መንገድ ብዙውን ጊዜ አድካሚ፣ እንደሆነ ያስረዳል ፡፡ በግለመር መማር ሂደት የተማሪዎች በተለያዩ ዕለታዊ ክንውኖች የሚያገኟቸውን ብቃቶች፣ አመለካከቶች፣ ወደ ስነ-ትምህርታዊ ችሎታ ለመለወጥ ጥረትየሚያደርጉበት ሂደት ነው፡፡ በግለመር መማር ወቅት ራስን የመቆጣጠር ወይም የመምራት ሂደት ትልቅ ተግባር ሲሆን ተማሪዎች ድክመታቸውን እንዲመለከቱ ከመሆኑም በላይ የሚጠቀሙባቸውን የመማር ዘዴ ውጤታማነት በአግባቡ እንዲመለከቱና ተማሪዎች እንዴት እንደሚማሩና የመማር ዘዴዎችን እንድላዩ ይራዳል፡፡ Eric (2011)ተማሪዎች የመማር ዘዴዎችንና የትምህርት ግቦችን በማቅድና በአግባቡ በመተርጎም የመማር ችሎታቸውን እንደሚያሻሽሉና የአንብቦ መረዳት ችሎታቸውንም እንደሚያስድጉ ያገልጻሉ፡፡

## 2.7. የአንብቦ መረዳት ችሎታ ደረጃ አሳጣጥ

አንብቦ መረዳት ችሎታ የተማሪዎችን ተግባር ለመመዘን የሚጠቅመው የአንብቦ መረዳት ፈተና ነው፡፡ ተፈተኞቹ ከፈተናው በሚያገኙት ውጤት በመነሳት የአንብቦ መረዳት ችሎታቸው በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ ማገናዘብ ይቻላል፡፡ አንደ ተማሪ በአንብቦ መረዳት ፈተናው የተገኘውን ውጤት 70% ከሆነ አንብቦ የመረዳት ችሎታው በቂ ነው የሚባልባት ደረጀ ላይ እንደሚገኝ እና በቂ የአንብቦ መረዳት ችሎታ አለው የሚባለው ተማሪው በለመደው ፍጥነት በማንበብ 70% ውጤት ሲኖረው ነው፡፡ የተፈታኙ ውጤት 50% እና ከዚያ በታች ከሆነ ችሎታው ዝቅተኛመሆኑን Najva(1975.144) ይገልጻሉ፡ ተማሪው የተሰጠውን ፈተና ከ70-80%የሚያስመዝግብ ከሆነ በቂ የአንብቦ መረዳት ችሎታ አለው፡፡ እንዲሁም ከ50-60% ያለው ችሎታ ዝቅተኛ ደረጃ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

ተጨማሪ Kavale (1979.27) ተማሪ የአንብቦ መረዳት ፈተና ከ90 እና ከዚያ በሚበልጥ ከመቶ % ከገኛ ተማሪ ከፍተኛ የአንብቦ መረዳት ችሎታ አለው፡፡ ከ75-90% ደረጃ ያለው ተማሪ የበቃ አንብቦ መረዳት ችሎታ ሲኖረው ከ75% በታች ዝቅተኛ ችሎታው መሆኑን ይገልፃሉ፡፡ ከላይ ያለው ሀሳብ የአንብቦ መረዳት ችሎታን ምሁራን የተለያዩ የደረጃ አሳጣጥን ባሳዩት መነሻ ተማሪዎች በተመዘኑት የአንብቦ መረዳት ፈተና ውጤት መነሻ በማድረግ ደረጃዎችን በሚከተለው ሂደት ማስቀመጥ ተገቢ ይሆናል፡፡ ይኸውም ከ10-9 ወይም 100-90% ከፍተኛ፣ከ8-7 ወይም ከ80-70 መካከለኛ እንደሁም በቂ ከ60-50 በታች ዝቅተኛ እንደሚሆን መገመት ይቻላል፡፡

## 2.8. የጥናቱ ንድፈ ሀሳባዊ መነሻ

ጥናቱ በሁለት ንድፈ ሀሳቦች ላይ ጥናቱ የተመሠረተ ሲሆን እነዚህም የግንባታዊያን የመማር ትውረት (constractivesm theory) ንድፈ ሀሳብ እና ማህበረ አእምሮታዊያን የመማር ትውረት (social cognitive theory) ንድፈ ሀሳቦች ናቸው፡፡ ይህ ጥናቱ በእነዚህ ንድፈ ሀሳቦች ላይ የተመሰረተበት ምክንያት ንድፈ ሀሳቦቹ ግለመር መማርና የአንባቦ መረዳት ችሎታ ግንኙነቱን የሚደስሱ በመሆናቸው ነው፡፡

ግንባታዊ የመማር ትውረት ተማሪዎች በግላቸው የመማር እና የዕውቀት ግንባታ ድጋፍ ላይ ያነጠጥራል፡፡ አንድ ሰው እንዴት መማር ይችላል?እንዴት ሊያውቅ ይችላል? ከሚለው አመለካከት በመነሳት የግላቸውን የመማር ደረጃና የዕውቀት ግንባታ በምን ሁኔታ እንዳለው ይዳስሳል፡፡

ዕውቀት የሚገነባው በቀደመ ዕውቀት ላይ በመመሰረት ነው፡፡ ተማሪዎች የመጀመሪያ ወይም የቀደመ ዕውቀታቸውን በማነሳሰትና መግባበት በመፍጠር የቀረበው ትምህርት አካል በማድረግ ትምህርቱ ማነሳሳት እንዲኖራቸው በትኩረት የሚሳተፉ የንቁ የጉዳዩ አካል ወይም ባለቤት በማሳየት፣መምህራን ደግሞ የመማር ልምድ በመፍጠር ተማሪዎች በተለየ አቅጣጫ እንዲሁም ከመምህራኑ ግምት በተለየ ሁኔታ መማር እንዲችሉ በማድረግ ተማሪዎችን፣ የመጠናከር፣መማር ማስተማሩን ምቹ የማድረግ፣ ኃላፊነት የመቀበል እና ተማሪዎች ነፃ ሆኖ ዕውቀት የሚያግኙበትን መንገዶችን መማቻቸት እንዳለባቸው (Evangelisto, 2002,1) ያስረዳሉ፡፡ Rowell & plamer (2007,4) ግንባታዊነት አእምሮአዊ ግንባታዊነት እና ማህበራዊ ግንባታዊነት በመባል ለሁለት እንደሚከፈል ያስረደሉ፡፡ እንደ ምሁራኑ አገለለጽ መሰረት አእምሮታዊ ግንባታዊነት የሚያሳይ አንድ ተማሪ ዕውቀት የሚፈልቀው ፍላጎቱን እና የተለያዩ ምኞቱን ለመተግባር በሚያደርገው እንቅስቃሴ እንደሆነ እና መማርም በዋናነት የሚያተከረው በግለሳበዊ ጥረት ላይ እና የማህበራዊ ግንባታዊነት የትኩረት መንገድ ደግሞ በትምህርታቸው የተሻሉ ተማሪዎች ዝቅታኛ ችሎታ ያለቸውን ተማሪዎች እንዲያበረታቱ ማህበራዊነትን መማቻቸትና ማዳራጃት እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ ግንባታዊያን ማንበብ አንባቢዎች በአዕምሮዊ ዕውቀት መዋቅራቸው ካለው ዕውቀት በመነሳትና ከጽሑፍ ከተገኘው አዲስ ሀሳብ ጋር በማጣማር ትርጉምን የመገንባት ሥራ እንደሆነና በዚህም ሂደት አንባቢዎች ከሚነበበው ከምንባቡ ግብ ጋር ግንኙነት በማድረግ ጽሑፉን ለመረዳት ጥረት እንደሚያደርጉ (Rowell& palmer, 2007,3) ያብራረሉ፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ጥናቱ የሚያተኩረው በማህበረ አእምሮታዊ የመማር ንድፈ ሀሳብ ላይ

ነው።Lencion (2013,9) የተማሪዎች ሚኖሩበትን ማህበረሰብ፣በመማር ክፍል ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች መምህራን ከተማሪዎችና ተማሪዎች ከመምህራን ጋር በሚኖራቸው ነው ግንኙነት በተማሪው ማንበብ ላይ ተፅዕኖ እንደሚኖረው በመመልከት ተማሪዎች የሚማሩት እነሱን በሚወክል ዕውቀት ወይም የሥራ ቆይታ በመግለጽ መሆኑን እንዲሁም የተለያዩ ተግባራትንና አመለካከትን የሚማሩት ከሌሎች ምሳሌ በማየትና የልጆች አእምሮዊ ዕድገት የተመሰረተው የተሻለውን ከሌሎች ጋር በሚኖረው ግንኙነት በመሆኑ ከእኩያዎቻቸው እና ከእነርሱ ከፍ ካሉ ክሂሎት እና ዕውቀት ካለቸው እኩያዎቻቸው ጋር ሲተባበሩ እና ከእነርሱ የበለጠ  እንደሚማሩ እና የተማሪዎች ዕውቀት፣አሳተሳሰብ፣ አመለካከትና ተግባር ከሌሎች ጋር በሚሆነው መስተጋብር እንደሚጸባረቅ ይገልፃሉ።

ማህበራ አእምሮታዊያን የመማር ዘዴዎች ከግለሰብ ሁኔታ ይመለከታሉ።በራስ ውጤታማነት ላይ የሚኖር ግለ ግምት በማጎልበት ተማሪው ራሱን ችሎ ተግባራትን ለማከናወን ችሎታውን የሚመለከትበት ነው።ለግለ ውጤታማነት መሠረቱ ለራስ የሚሰጥ ግለ ግምት ነው።ተማሪ ራሱን ችሎ ተግባራትን ለመካናውን ለሚያስችለው ችሎታው ያለው አመላካከት ሲሆን ተማሪዎች ከፍተኛ የሆነ በግል ውጤታማነት ላይ የሚኖር ግለ ግምት ደረጃ ላይ ሲደርሱ ዘዴዎችን የመጠቀም አቅማቸው የበለጠ እየጎለበተ እና በመማር ወቅት በግል መተማመን(self efficay) ወሳኝ ሲሆን ተማሪዎች አንዳች የተለየ ግብ ለማሳከት ችሎታ እንዳላቸው የሚያሚኑበት እንዲሆን Bandura(1986,32) ያስረዳሉ።ተማሪዎች በግል መተመማናቸው በጨመረ ልክ እንደገና በአዲስ ሁኔታ ለመማር የበለጠ ይነሳሳሉ፣በቀጠይነት ሌሎችም ተግባራትን ከሌሎች በተሻለ መልኩ ለመስራት እንደሚነቃቁ ያስረዳሉ።እንደ Chamot (1989,24)አገላለፅ በማህበረ አእምሮታዊ ንድፈ ሀሳብ ስር ከሚከተቱት የመማር ዘዴዎች መካከል አእምሮዊ የመማር ዘዴዎች  ይጠቀሳሉ።የዘዴዎች ትኩረት ደግሞ በግለዊ የመማር ተግባራት ላይ ነው።Oxford (1990) እና Brown(1994) ተማሪዎች የራሳቸውን ስራ በራሳቸው እንዴት አድርገው በራሳቸው መሰረት እንዳለባቸው እና ከሌሎች በወሰዱት ልምድ መሠረት የማንባብ ተግባራትን እንዴት አድርገው በራሳቸው መፈጸምና መለመማድ እንዳለባቸው እንዲሁም ራሳቸውን የግንዛቤ ሂደት እና አስተሳሰበቸውን በማስተዋል በንባብ ትምህርት ሂደት ላይ የሚያጋጥሙ የንባብ ጊዜ ችግሮችን በማቀድ፣በመቆጣጠርና በመገምገም እንዴት መፍታት እንዳለባቸው ያብራራሉ።ሲጠቃለል ግንባታዊያን የመማር ተግባርን ከግለሳቦች እውቀት ግንባታ አንፃር ሲመለከቱ፦ማህበረ አእምሮታዊያን ደግሞ ነገሮችን የምንማረው ከሌሎች ሰዎች ጋር በምናዳርገው ግንኙት ወይም ደግሞ ሌሎችን በመመልከት ነው።ተማሪዎች ከሌሎች

በሚወስዱት ልምድ መሠረት የማንበብ ተግባራትን በራሳቸው ይወጣሉ የሚል አመለካከት ያንፃበርቃሉ፡፡የግንባታዊንም ሆነ የማህበረ አእምሮታዊያን ንድፈ ሀሳቦች በቀጥታ ግለመር መማርን ይደግፋሉ፡፡ግለመርነት የግል ተግባር እንዳመሆኑ መጠን ለግለ ውጤታማነት መሰረት ነው፡፡በመሆኑም የንባብ ስራ ግለሰባዊ በመሆኑ ግለመርነትን ይጠይቃል፡፡በግለመር ዘዴ የተገዛ የንባብ ሂደት የአንብቦ መረዳት ችሎታን የበለጠ ያጎለብታል፡፡

## 2.9. የግለመር መማር ሞዴሎች

### 2.9.1 የዚመርማን ግለ መር መማር ሞዴል (Zimmerman's Process Oriented Model Of Self-Regulated Learning )

ይህ ሞዴል ግለ መር መማር ከግል የምመነጭ ግለሳበዊ ግብና እቅድ የያዘ ሀሳብ ፣ ድርጊትና ስሜት እንደሆነ በመጥቀስ ግለመርመማር ዘዴዎችን ለማሳደግ የተለያዩ ሂደቶችን በቅደም ተከተል መከናወን እንደሚገበ ተገልጾል ፡፡ እነዚህም ሶስት ሂደቶች ፦ የዕቅድ ትግባራ፣ የራስ ምልካታ እና የውጤት ቁጥጥር ናቸው ፡፡ ተማሪዎች የቀዱትን ይተገብራሉ፣ አፈፃፀማቸውን ይመለካታሉ ወይም ይገመግመሉ ፤ የግላቸውን ብቃት በመለየት ወይም በመፈተሽ ለግለቸው ውሳኔ ይሰጠሉ ፡፡ በግለ መር የመማር ሂደት የተማሪዎች ተግባር የሚያጠኑትን ይዘት ማራጋገጥ ፣ ለመማር የሚያስቸግራቸውን መገምገም ፣ ለውጦችን መከታተልና የመማር ውጤታቸውን መቆጣጠር ነው ፡፡ ይህ ሞዴል ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ዘዴዎችን እንዲያሻሽሉ ማገዝ ፣ የአንብቦ መረዳት ዘዴዎችን የሚማሩባቸውን አላማዎች መግላፅ ፣ ተማሪዎች ራሳቸውን መቼና እንዴት መገምገም እንደላባቸው መግላፅና ተገቢ ግላዊ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ማቀድ ፣ ዘዴዎችን መጠቀምና ግሉን በመገምገም ማስተካከል እንዳለበቸው እና ተማሪዎች ሁልጊዜ ግለ መር መማር ዘዴዎችን አንድ በአንድ መጠቀም ከለመዱ ራሳቸውን ችለው ተግባራትን መስረት እንደሚችሉ ይገልጻሉ፡፡

### 2.9.2.. የፒንቲርችስ አላባ ተኮር የግለመር የመማር ሞዴል (Pintrich's Component Model of Self-Regulated Learning)

በዘህ ሞዴል ግለ መር መማር ዘርፈ ብዙ ተግባር መሆኑን ይዳስሳል ፡፡ የሚያተኮረውም ግለመር መማር በርካታ ተግባራትን ማከናውን የሚያሻው መሆኑን ያሳያል ፡፡ እንዲሁም

በግለመር መማር ጊዜ  አእምሮን ፣ ስሜትን ፣ ተግባርን ፣ ግብን ፣ የመማር ዘዴን ፣ የመማር ፍላጎትን መቆጣጠርና ራስን የመፈተሽ ተግባራትን ተማሪዎች መፈፀም እንደለባቸው ይዳስሳል ። በዚህ ሞዴል መነሻ ተማሪዎች የመማር ግቦቻቸውን ያቅዳሉ፣ እቅዶቻቸውን ያዘጋጃሉ ፣ የመማር ዘዴዎችን ይመርጣሉ ፣ የመማር ሂደቶቻቸውን ይቆጣጠራሉ ፣ የመማር ውጤታቸውንም ይገመግሙና የግለቸውን ጠንካራና ደካማ ጎኖቻቸውን በመለየት ለቀጠዩ መማር እንደሚዘገጁ ተገልፆል ። ግለመር የመማር ሂደት እንደ ትምህርቱ ይዘት እንደ ተማሪዎች የግል ጥረትና ግላዊ ብቀት ሊላያይ ይችላል ። የተማሪዎች የትምህርት ውጤት በግለመር የመማር ዘዴ አጠቃቀማቸው ይታወቃል ።በግለመር የመማር ዘዴ የሚካተቱ ደረጃዎችም ግብ ማስቀመጥ ፣ የራስን አካሄድ መቆጣጠር ፣ ማደራጀትና የግል ተግባር  ማድረግ እንደሆኑ በሞዴሉ ተገልፆል ።

### 2.9.3. የግለመር መማር ደረጃና ሂደት ሞዴል

ይህ ሞዴል የተገለጻው ሀሳብ ግለ መር መማር ደረጃና ሂደት ምን ምን እንደሆነ የተገለፃበት ነው ። በዚህ ሁኔታ በቅዲሚያ የግለመር መማር ደረጃ የእቅድ ትግባራ ሲሆን ሂደቱም ተማሪዎች ለውጤታቸው ስኬት ዕቅድ ያዘጋጃሉ ፣ እቅዶቻቸውንም በትኩረት የከናውነሉ ። በሁለተኛው የግለመር መማር ደረጃ ብቃትን የሚገልጽ ሲሆን ሂደቱም መተግባሪና መቆጣጠርን ያሳየል ። በመጨረሻው የግለመር መማር ደረጃ መፈተሽና መገምገም ሲሆን አቅጣጫም  የግል እይታ በማድረግ ጥንካሬና ድክመት የሚፈተሽበት እንደሆነ በሞዴሉ ተገልጾል ።

### 2.10. ማንበብና አንብቦ መረዳት ችሎታ

ማንበብ ከመቀበያ ክሂሎች ውስጥ የሚመደብ ሲሆን ለክሂሉ መዳበር ተማሪው የሚማሩትን ቋንቋውን በስርዓት መጠቀም እንዲችሉና ሰፊ የቋንቋ አስፈላጊ ግብዓቶችን ማቅረብ የሚያስችላቸው ሆኖ በክፍል ውስጥ በመማር ማስተማር ጊዜ የሚሰጠው የአንብቦ መረዳት ትምህርት ዓላማ ያለው መሆን እንዳለበት እንደሁም አላማው በግልጽ የታወቀ የንባብ ጊዜ ትምህርት ደግሞ የማንበብ ችሎታን እንደሚያሳድግ፣ የተማሪዎቹ የንባብ ችሎታ መጠናከሩ ጥሩ የቋንቋ ተጠቃሚዎች እንዲሆኑ እንደሚያዳርግ ተጨማሪ ሌሎች የትምህርት ዓይነቶች የተሻለ ውጤት እንዲኖር ከማድረጉም በተጨማሪ የዕውቀት አድማስን ለማስፋት ከፍተኛ ጠቃሜታ በግልጽ የሚታወቅ ንባብ እንደሚያመቻች (ሰለሞን፣ 1994፣51) ይገልፃሉ። ማንበብ በእይታ መገንዘብ ወይም አካላዊ እንቅስቃሴና ለአዕምሯዊ ተግባርን የማከናወን

ሂደት እንደሆን፣የእይታ ተግባር ድምፅን ወይም ዋና መልዕክትን የወከሉ ትዕምርቶችን የማጥራት፣ትርጉማቸውን የመለያት፣በዓይነህልና ማስተዋልና ተግባሩን በአዕምሮ የመካናውን ተግባሪ መሆኑን አእምሮአዊ ተግባሩ ደግሞ እንድሁም በእይታ የተገኘሁን መረጃ የመተግባር በአንባቢው አዕምሮ ውስጥ የሚከናወነውን፣ የማመዘዘን፣ የመለየት፣ የማመሳከር፣ የመፈተሽና የማወቅ ሂደቶችን እንደሚያካትት (Harmar, 1991,153) ያብራረሉ። ማንበብ ግላዊ ተግባር መሆኑን በርካታ ምሁራን ይስማመበታል። አንባብው የቋንቋውን ድምፆችና ቃላት ንበት (አጠራር) ለመለማመድ ካልሆነ በስተቀር አብዛኛው በግልጽና በለሆሳስ የሚከናወን መሆኑን (Davies 1995.1)ይገልፃሉ። "አንብቦ የመረዳት ችሎት ማለት ከተጻፈው ጽሑፍ ውስጥ የሚፈለገውን መረጃ ለይቶ በማውጣት ጽሁፉን የመገንዘብ ሂደት ነው። አንባብው በተገቢው የሚፈለገውን መረጃ የሚለይበት ተራ ያልሆነ ጥልቅ ግንዛቤን የሚያመለክት ነው"(Williams,1990,3)። Grellet (1981,3) "አንብቦ መረዳት ማለት ከሚነበበው ጽሁፍ ውስጥ አንባቢው እስከሚችለው ድረስ በብቃት መረጃ ማገኘት መቻል ነው።" ከዚህ ሀሳብ መረዳት የሚቻለው አንብቦ መረዳት ችሎታ አንድን ምንባብ ከራሱ ጋር በማስታያየት ለምንባቡ ትርጉም የመስጠት ሂደት መሆኑ ነው ።

## 2.11. የአንብቦ መረዳት ችሎታ አስፈላጊነት

ንባብ አንድ የተጸፈውን ጽሑፍ ወይም መልዕክት ያለውን ሀሳብ ወደ ድምፃዊ ቋንቋ የመተርጎም ተግባር ነው። ቃላትን ከመረዳትና ትርጎም በመስጠት ወደ ተሻለው ደረጃ በማስተዋልና በማቀነባበር ደረጃ ከፍ ወይም እያደገ የሚሄድ የመሳብ ዋና አዕምሯዊ ተግባር ውጤት ነው። በመሆኑም በክፍል የመማር ማስተማር መንገድ በማከሄድ የቋንቋ ክሂሉን ማሳደግና ማንበብን ልምድ በማድረግ መያዝ አስፈላጊ ነው። ማንበብ ልምድ በመሆን ሊያዝ ወይም ሊተግበር የሚቻለውም ከታች ወይም በጀማሪ የትምህርት ዕርከኖች የበላፀጋ የማንበብ ክሂል በመሆኑ በደረጃው ተገቢውን ልምምድ ማድረግ ወሳኝነት አለው። Greenwood (1981,89) Ellis (1980,141) አንብቦ መረዳት ችሎታ የተማሪዎችን የቋንቋ እውቀት ከፍ በማድረግ የተሻለ መረዳት እና በስፋት ለማስተዋል ያግዛቸዋል። በጽሑፍ ውስጥ ሊተላለፍ የሚፈላገውን መልዕክት አቅም በቸለው መጠን እንደረዱ የሚያደረገቸው ሲሆን የቃላትን ፊቺ በቀላሉ እንዲገነዘቡም ያግዛቸዋል። በተጨማሪ የአንብቦ መረዳት ችሎታ የአንድን የተጻፈውን ጽሁፍ በግል እና በድብቅ ያለውን መልዕክት ለመረዳት እና የጽሁፍን ቅደም ተከተለዊ የሀሳብ ደረጃ ወይም ፍሳት ለመረዳት የአንብቦ መረዳት ችሎታ እንደሚያስፈልግ ያስረዳሉ።

## 2.12. አንብቦ መረዳትን በግል መምራት

እንደ Zimmerman (1990) አገላለፅ አንብቦ መረዳትን በግል ለመምራት የማንበብ ክሂልን በተለያዩ መንገድ ማጎልበት ያስፈልጋል፡፡ መረጃዎችን ለማቀናጀት ዕቅድ ማዘጋጀት፣ በማንበብ ወቅት ዕቅድን በተግባር የመለወጥ ሂደትን የተለያዩ ዘዴዎችን ማዳባር ሲሆን ከማንበብ በኋላ ጠቃሚ መረጃን አስፈላጊ ካልሆነው ለመለየት የሚያስችሉ ጥያቄዎችን መስራት እንደሚያስፈልግ ይገልፃሉ፡፡ Block(1997) አንብቦ መረዳትን ለማዳበርና በግል ለመምራት ተማሪዎች ስለሚያነቡት ጉዳይ ጥያቄ መጠየቅ ፣መገመት፣ መተንበይ፣ ማብራራት፣መተርጎም፣ምስል መፍጠር፣ማጠቃለልና የመሳሰሉ የአንብቦ መረዳት ዘዴዎችን ተማሪዎች ሊለማመዱ እንደሚገባ ያብራራሉ፡፡

## 2.13. ግለመር የመማር ዘዴ ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያለው ዝምድና


አንድ ሰው አንድን ጽሁፍ አንብቦ ለመረዳት ችሎታው በግለመር መማር ዘዴ በመተግበር ላይ መሠረተ ያደረገ ነው፡፡ ስለዚህ አንድን ጽሑፍ አንበቢው ለመረዳት ችሎታ የግለመር መማር ዘዴዎችን ከመተግባር ጋር የተያያዘ ነው፡፡ በመሆኑም የአንድን ምንባብ አንብቦ የመረዳት ችሎታ የግለመር የመማር ዘዴዎችን በቀጥታ ከመጠቀም ጋር የተገናኘ ነው፡፡ አንባቢዎች በቀደምት ዕውቀታቸው እና አዲስ በሚያነቡት ይዘት መካከል ትስስር መፍጠር የሚስችሏቸውን ግለመር የመማር ዘዴ ካልተጠቀሙ አንበቢው አዲስ ዕውቀት ለማደራጃትና ለመረዳት ሊያግዛቸው የሚችል መረጃን የማግኛት አቅጣጫ ዝቅተኛ መሆኑን (conley. 1992) ይጠቅሳሉ፡፡ አንብቦ የመረዳት ችሎታና የግለመር መማር ዘዴዎች እርስ በርስ የተቆራኙ ከመሆናቸውም ባሻገር ከፍተኛ የሆነ አወንታዊ ዝምድና አለቸው፡፡ አንብቦ የመረዳት ችሎታ በግለመር መማር ዘዴዎች የሚዳብር በመሆኑ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ከፍ ሲል ደግሞ የግለመር መማር ዘዴዎችን የመጠቀም ሁኔታ ይጨምራል፡፡

## 2.14. የጥናቱ ፅንስ ሀሳባዊ ማእቀፍ

ጥናቱ ግለመር የመማር ዘዴ ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያለውን ዝምድና የሚደስስ ሲሆን የሚተገበረውም ከታች በቀረበው በስዕሉ የታየውን ፅንሳ የሀሳባዊ ማእቅፍ መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እንዲሁም ከታች የቀረበው ፅንሳ ሀሳባዊ ማእቀፍ የሚያስረዳን ከታች ወደ ላይ ስንመለከት ተማሪዎች ለግለመር የመማር ዘዴዎች ያሉዋቸውን ግንዘቤ ከመማር ዘዴ እስከ ግብ ማስቀመጥ ምን እንደ ሚመስል ያሳያል፡፡ ከግብ ማስቀመጥ ከመማር ፍላጎት እንዲሁም የመማር ዘዴን ስዕላዊ መግለጫ መነሻ አድርጎ ከግራ ወደ ቀኝ አግድም

(Horizontal) የሚያመለክቱት ቀስቶች የግለመር መማር ዘዴዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታን የማሳደግ ድርሻ የሳያሉ፡፡ መነሻቸውን ግብ ማስቀመጥ የመማር ፍላጎት እንዲሁም የመማር ዘዴ በማድረግ ወደ አንብቦ መረዳት ችሎታ የሚያመለከቱት የቀስት ምልክት ደግም ንዑሳን የመማር ዘዴዎች ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያሉዋቸውን ዝምድና የሚየሳይ ናቸው፡፡

ይህ ስዕላዊ መግለጫው የግለመር መማር ዘዴዎች ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያለውን ግንኙነት ወይም ዝምድና ለማሳየት የቀረበ ነው፡፡ ከታች ያለው ምስዕል ዘመርማን (2000)፣ ኤርክ (2011) እና ቦክርሲት(1999) (Learning preformance scale) ለመቅረጽ ከተዘጋጀው መሻሽያ በመድረግ 2015 ዓ.ም. የጥናታዊ ጽሁፍ አቅረቢ የቀረበ ነው ፡፡




ከፍ ብሎ እንደተከለጸው ከጥናቱ ፅንስ ሀሳባዊ ማእቀፍ ተነሰቶ ወደየት እንደሚሄድ የሚያሳይ ነው፡፡ ከላይ በማእቀፍ ለመጠቀም የመጀመሪያዎቹ ከበለ አራት ጎን መአዘን ሬክታንግልን (ምስል)መነሻ ያደረጉት ባለ ሶስት የግለመር መማር ንዑሳን ዘዴዎችንና የመማር ዘዴዎች ከአንብቦ መረዳት ወደ ግራ ሶስት ትንንሽ መእዘን ምስሎች ትሬንግሎችን መነሻ በማድረግ ወደ ክብ ከሆነው ወይም ዜሮ በሚመስል የሚያመለክቱት ባላ ሶስት ቀስቶች ንዑሳን የግለመር መማር ዘዴዎችና የመማር ዘዴዎች ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያላቸው ተዛምዶ የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ወፍራም የሆኑ በለሶስት አቅጣጫ ቀስቶች ወደ ባሊዲ በሚመስል መእዘን ምስል የሚመለክቱ ሲሆኑ ግለመር የመማር ዘዴዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታን የማሳደግ ድርሻቸው ምን ያህል እንዲሆነ የሚሳዩ ናቸው፡፡

ከላይ ከጥናቱ ፅንስ ሀሳባዊ ማህቀፍ በአጠቃላይ የሚንገነዘበውየጥናቱ አጠቃላይ ሁኔታ

ከየት ተነስቶ ወደየት እንደሚሄድ እንዲሁም በጥናቱ ውስጥ የሚደሳሱ ሀሳቦች የሚኖራቸው የእርስ በርስ የግንኙነት ሁኔታ ጠቅላል ባለ መልኩ መገነዘብ ይቻላል።

## 2.15. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ርዕስ ሥር የሚቀርቡት ግለመር የመማር ዘዴ አንብቦ ከመረዳት ችሎታ ጋር ያለውን ዝምድና በተመለከተ ቀደምት የተጠኑ ጥናታዊ ጽሑፎች ሲሆን ጥናቶቹንም ከዚህ ጥናት ጋር ያለቸውን ተመሳሰይነት እና ልዩነት ለማሳየትም ይሞከራል።

ማስተዋል ውብቱ (1989)" የከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ" በሚል ርዕስ ጥናት ያካሄዱ ሲሆን በጥናቱ ውስጥም ትኩረት የተደረገው የተማሪዎች አንብቦ መረዳት ችሎታ ዝቅተኛ መሆን ምክንቶች ምንምን ናቸው? የሚል ነው። ጥናቱን ሲያካሄዱ የተጠቀሙት መረጃ መሰብሰቢያ መሣሪዎች ምልከታ፣ የፅሁፍ መጠይቅና፣ የአንብቦ የመረዳት ፈተናዎች ናቸው።

እንዲሁም የመምህራን የትምህርት አሳጣጥ ሁኔታና የመማሪያ መፅሐፍት ችግሮች ለአንብቦ መረዳት ችሎታ ዝቅተኛ መሆን ዋና ዋና ምክንያቶች እንደሆኑ የጥናታቸው ውጤቱ ያሳያል። የማስተዋል ጥናት ከዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ ጋር የሚመሳሰለው ከይዛት አኳያ ስለአንብቦ መረዳት ችሎታ በመነሳቱ የመረጃ መሰብሰቢያ የጽሑፍ መጠይቅ፣ የአንብቦ መረዳት በመጋራቱ ነው። የሚለየው ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ ግለመር መማር ዘዴ አንብቦ ከመረዳት ችሎታ ጋር ያለውን ተዛምዶ መፈተሽ በመሆኑ ነው። ሌላው ጥናቶቹ ከተጠኑበት ጊዜና፣ ቦታ አንፃርም ልዩነት አለቸው።

ባንቺ አምላክ ፈጣን (2013) "አእምሯዊ የመማር ብልሃቶችን በግልፅ ማስተማር አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማጎልበት ያለው አስተዋፅኦ "በሚል ርዕስ ጥናት ያካሄደች ሲሆን ትኩረቱም አእምሯዊ የመማር ብልሃቶችን በግልፅ ማስተማር አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማጎልበት ያለው ሚና መመርመር ነው ። ጥናቷን ከግብ ለማድረስም ፈተና እና የጽሁፍ መጠይቅ በመረጃ ማሰቢሳቢያ መሳሪያነት ተጠቅማለች። የዚህ ጥናት የመማር ዘዴዎች በመነካካቱ፣ በአንብቦ መረዳት ችሎታ በመነሳቱ እና የፈተና እና የጽሑፍ መጠይቆችን መጠቀሙ ሲያመሳስለው የሚለየው የግለመር መማር ዘዴ ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያለው ተዛምዶ በመፈተሽ የሚያተኩር በመሆኑ ነው።

ፋሲካና አገኘሁ (2008) በጎንደር ከተማ በፋሲለደስ መሰናዶ ትም/ቤት "በትብብር መማር አንብቦ በመረዳት ችሎታና ፍላጎት ላይ ያለውን ሚና መፈተሽ "በሚል በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተሰረው ጥናት ሲሆን ከግብ ለማድረስ የተጠቀሙ የመረጃ መሣሪያዎች

የአንብቦ መረዳት ፈተናና የጽሑፍ መጠይቅ ሲሆን መረጃዎች በነፃ ናሙና ቲ-ቲስት ተተንትኑዋል ከእኔ ጥናት ጋር ሲያመሳስለው የሚለው የእኔ ጥናት ግለመር መማር ዘዴ ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ሲዳስስ ይህ ደግሞ በትብብር የመማርን አንብቦ መረዳት ችሎታና ፍላጎት አጣምሮበመመልካቱ ነው፡፡

አስተር አስረት (2010)" የቤተሰብ ዳራ የአንብቦ መረዳት ችሎታን የመተንበይ ድርሻ በሚል ምርምር ያካሄዳች ሲሆን ጥናቷ ለማካሄድም የጽሁፍ መጠይቅ፣ፈተና እና የቡድን ውይይት የመረጃ መሰብሳቢያ መሳሪያዎችን ተጠቅመለች፡፡ ከዚህ ጥናት ጋር ስለ አንብቦ መረዳት ችሎታን ፈተና እና የጽሑፍ መጠያቅን ለመረጃ መሰብሳቢያነት መጠቀሙዋ የሚያመሳስለው ሲሆን የሚለያየው ደግሞ የቤተሰብ ዳራ ከአንብቦ መረዳት ጋር አቆረኝተ የደሳሰች ሲሆን የእኔ ጥናታዊ ጽሑፍ የግለመር መማር ዘዴ ከአንብቦ መረዳት ጋር ያለውን ዝምድና የሚመለከት ነው፡፡ በተጨማሪ የቡድን ውይይት መረጃ መሰብሳቢያ መሳሪያ አለመጠቀሙ ልዩ የደረገዋል፡፡

ታደሰ ዳርገው፣ ማረው አለሙና ሙሉጌታ ተካ (2010)"የረስ መር መማር ብልሀቶች አንብቦ የመረዳት ችሎታና ብልሀቶች አጠቃቀምን የማሳደግ ሚና፤በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት" በሚል ርዕሰ ጥናት የካሄዱ ሲሆን የጥናታቸው ዓላማም የራስ መር መማ ብልሀቶች አንብቦ የመረዳት ችሎታንና የብልሀቶችን አጠቃቀም የማሳደግ ሚና መመርመር ነው ፡፡ጥናቱ የተሄደው በጎንደር ከተማ አስተዳደር በልዑል አለማየሁ ቴዎድሮስ 1ኛ ደረጃ ትም/ቤት በ2010 ዓ.ም በ7ኛ ክፍል ትምህርታቸውን በሚመሩ ተማሪዎች ላይ ነው ፡፡ ይህንን ጥናት ከግብ ለማድረስ የተመረጡት መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የአንብቦ መረዳት ፈተናና የጽሁፍ መጠይቅ ሲሆኑ በእነዚህ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አማካኝነት የተሰበሰቡ በአይነታቸው ተደረጅተው በአማካይ ውጤትና በልይይት ትንተና ተተንትነዋል፡፡ የጥናታቸው ግኝት የሚያሳያው የራስ መር መማር ብልሀቶች የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታና የብልሀቶች አጠቃቀም ከማሻሸል አኳያ ጉልህ ሚና እንዳለው ሲያመለክት በራስ መር መማር ብልሀቶችና አንብቦ መረዳት ችሎታ መካከል አዎንታዊ ተዛምዶ እንደለም ጥናቱ ውጤት ያሳያል፡፡ ይህ ከዚህ ጥናት ጋር የሚማሳስለው የራስ መር መማር ብልሀቶችን አጠምሮ መዳሰሱና ለመረጃ መሰብሳቢያነት የአንብቦ መረዳት ፈተናና የጽሁፍ መጠይቅ መጠቀሙ ነው ፡፡ጥናቱ ከእኔ ጥናት የሚለያው ራስ መር የመማር ብልሀቶች አንብቦ የመረዳት ችሎታና የብልሀቶችን አጠቃቀም ማሳደግ በሚል ርዕሰ ላይ ትኩረት ያደረገ በመሆኑ ነው ፡፡ የእኔ ጥናት ግን ግለመር የመማር ዘዴ ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያለው ተዛምዶ ምን እንደሚማስል በመፈተሽ ላይ ትኩረት ያደረገ ነው ፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

## 3. አጠናን ዘዴ

### 3.1. የጥናቱ ንድፍ

ይህ ጥናቱ ዓላማ ያደረገው የግለመር መማር ዘዴ ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያለውን ተዛምዶ መፈተሽ ነው፤ ጥናቱ የፒርስን ተዛምዷዊ (Correlation) መጠን መለኪያ ቀመር የምርምር ንድፈ ተካትሏል፡፡ ተዛምዳዊ ምርምር ንድፈ የተመረጠበት ምክንያትም በተላውጦች መካከል ያለውን የተዛመዱቡት መጠን ለማሳየት የሚጠቅም ዘዴ ነው፡፡ያለው(2009.341) በተለዋዋጮች መካከል የግንኙነት አቅጣጫና መጠን ለማመልከት ተዛምዷዊ የምርምር ንድፈ ከፍተኛ ጠቃሜታ እንዳለው ይገልፃሉ፡፡ ቅይጥ ጥናታዊ ዘዴን መተግባር ሲሆን ከፈተናና ከጽሁፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች በመጠናዊ ዘዴ ተተንትነው ቀርቦል፡፡ ጥናቱ "ገላጭ ስታትስቲክስን ተጠቅሟል፡፡ ያለው (2009፣254) “ገላጭ የስታቲክስ ዓይነት የተገኙው ሰፊ መረጃ በአንድነት ተጠቃልለው፣ተጨምቀው በሚወጡ ውስን ቁጥሮች አማካይነት የተጠኚዎቹን(የናሙናውን) አማካይ ባህርይ ለመግለጽ የሚሞከርበት ነው” ይላል፡፡

### 3.2. የናሙና አመራራጥ

#### 3.2.1. የጥናቱ ቦታ አመራራጥ

ይህ ጥናት የሚካሄደው በማእከላዊ ኢትዮጵያ  ክልል በሀዲያ ዞን በምዕራብ ባዳዋቾ ወረዳ በጃርሶ ኦንጆጆ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ነው፡፡ ይህ ት/ቤት ለአጥኚው ቅርብ በመሆኑ በአመቺ የንሞና ዘዴ ተመርጧል ይህም የሆነበት ምክንያት አጥኚው የሚያስተምረው በዚሁ ት/ቤት በመሆኑ ጥናቱን ሲያካሄድ ሊገጥመው ከሚችለው የጊዜና የገንዘብ እጥረት አንፃር አመቺ በመሆኑ እና አስተማማኝነት ያለው መረጃ ለማግኘት የተሻለ ሆኖ  በመገኘቱ ነው፡፡

#### 3.2.2. የተማሪዎች ናሙና አመራራጥ

በጥናቱ ላይ የሚሳተፉ ተማሪዎች የጃ/ኦንጆጆ 2ኛ ደረጃ ትምህርትቤት 2015 ዓ.ም የሚማሩ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡ ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ካሉ ተማሪዎች መካከል የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ብቻ ለጥናቱ አካላይ በዓለማ ተኮር ስልት በመጠቀም ነው፡፡ እነዚህ ተማሪዎች የተመረጡበት ምክንያት ተማሪዎቹ በትምህርት ደረጃቸውና በዕድሜያቸው ከዝቅተኞቹ የክፍል ደረጃዎች ከፍ ያሉ በመሆናቸው ግለመር የማመር ዘዴዎቹ በመተግባር ደረጃ ጥሩ ሊሆን ይችላል በሚል መረጃዎችን በጥሩ ሁኔታ ይሰጣሉ በሚል ተሳቢነት ነው፡፡

ያለው (2009፣136) አጥኚው የዓላማ ተኮር ንሞና ዘዴ የሚተገብሩ የጥናቱን ተሳታፊዎች እነማንን ብካተቱ የሚፈለገውንና ተገቢውን መረጃ ማግኘት  ይችላሉ? የሚሉ ነጥቦችን ከግንዘቤ ውስጥ በማስገባት የጥናቱን አላማ ከግብ ለማድረስ ሰዎችን ስንመርጥ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡

ለጥናቱ የተመረጠው ትምህርት ቤት ውስጥ በ2015 ዓ.ም ሁለት  የ9ኛ ክፍል ምድቦች ያሉት ሲሆን ሁለቱም ምድቦች የጥናቱ ተሳታፊዎች ናቸው፡፡ በነዚህ ክፍል ውስጥ ወንድ 47 ሴት 38 በድምር 85 ተማሪዎች ትምህርታቸው ይከታተላሉ፡፡ እንዲሁም በትምህርት ቤቱ ከሚማሩ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ውስጥ በዕድል ሰጭ የንምና ዘዴ ውስጥ የተከታተውን ቀላል የዕጣ ንምና ዘዴ በመጠቀም ወ 35 ሴ 30 ድምር 65 ተማሪዎች ዕጣ በማውጣት ተማሪዎች በጥናቱ መሳታፊ እንዲችሉ ተመርጠዋል፡፡ ይህ ቀላለ የዕጣ ማውጣት ንምና ዘዴ የተመረጠበት  ምክንያት ሁሉም የጥናቱ አካላይ ተማሪዎች በጥናቱ እኩል የመመረጥ ዕድል እንዲያገኙ በሚል ነው፡፡

## 3.3. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

ጥናቱን ከግብ ለማድረስ የተመረጡ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የጽሑፍ መጠይቅ እና የአንብቦ መረዳት ፈተና ነው፡፡

### 3.3.1.የጽሑፍ መጠየቅ

የጽሑፍ መጠይቅ ሌላው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ በመሆን ያገለገለ ሲሆን ተግባራዊ የተደረገውም ስለ ግለመር መማር ዘዴ ንዑሳን ክፍሎች መረጃ ለማግኘትና ስለ ግለመር መማር ዘዴዎች የተማሪዎችን ግንዘቤ ለመለከት ነው፡፡ የጽሑፍ መጠይቁ ተግባራዊ የተዳረገበት ምክንያትም የተጠኝዎችን የመማር ፍላጎት፣ግብ ማስቀመጥና የመማር ዘዴ አጠቃቀምን ለማሳየትና ከአንብቦ መረዳት ችሎታ አንፃር ያላቸውን ተዛምዶ ለመፈተሽ ነው፡፡ የጽሑፍ መጠይቅ አይነቶች ብዙ ሲሆኑ በዚሁ ጥናት ተግባራዊ የሆነው ውስን አጠያየቅ ነው፡፡ ይህ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የተመረጠበት ምክንያት አጭር በመሆኑ በተጠኝዎች ዘንድ ስለማመረጥ ነው፡፡ አለም (1997፣48) ውስን ጥያቄ፣ልቅ ከሆነው ጥያቄ ይልቅ በተጠኝዎች ዘንድ ይመረጣል፡፡ ምክንያቱም ተጠያቂው ጥያቄዎችን ለመመለስ ብዙ ጊዜ ካላመፍጀቱ ሌላ “ምን ብዬ ልመልስ እያለ የሚቸገርበትም ዓይነት ጥያቄ አይደለም” ይላሉ፡፡ ስለ ግለመር መማር ዘዴ ለመለከት ውስን የጽሑፍ መጠይቅ 24 ጥያቄዎች የያዘ ሲሆን ከጥያቄዎች ውስጥ ስምንት ከ1-8 ግብ ማሰቀመጥስምንት/ከ9-16/ የመማር ፍለጎትን ሰምንት/ከ17-24/የመማር ዘዴዎን ተማሪዎች የግለመር መማር ዘዴ እንዲለኩ ሆነው

ተዘጋጅቶ የቀረቡ ናቸው፡፡ የጽሁፍ መጠይቁን ተገቢነትን ለማረጋገጥ በመጀመሪያ በጥናቱ አማካሪ አስተያየት ተሰጥቶበታል፡፡ በተጨማሪም ሁለት የሁለተኛ ዲግሪ ያለቸው የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ገምግሞ አስተያየት ስጥተዋል፡፡ በተሰጠው አስተያየቶች መሠረት ሊያሻሙ ይችላሉ ተብሎ የሚገመቱ ቃላትና ሀረጋት በማስቀረት ተሻሽሎ እንዲዘጋጃ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም ለጥናቱ በልተመረጡ ሃያ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የሙከራ ጥናት ተደርጓል፡፡ የጥናቱ ሙከራ ውጤትን መነሻ በማድረግ ሦስቱንም የንዑሳን የግለመር መማር ዘዴዎችን አስተማማኝነት በፓይሌት test ተዘጋጅቶ በ(cronbach alpha) ቀመር በተናጠል ተሰልቶ ግብ ማስቀመጥ 0.89 የመማር ዘዴ፣ 0.95 የመማር ፍላጎት 0.88 ሆኖ ተገኝቷዋል፡፡ የጽሑፍ መጠየቁ ትክክለኝነት ቀደም በተገለጸው መልኩ ከተረጋገጠ በኋላ በተሳታፊ ተማሪዎች ቁጥር እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች መረጃውን በወረቀት ከመሙላታቸው በፊት ስለመጠይቁ መልስ የመስጠት ሂደት መመሪያ በማንበብ ግልጽ ያልሆነውን እንደጠይቁ ተደሪጎዋል፡፡ እንዲሁም በጥያቄ የተሳተፉ ተማሪዎች መጠይቁን ሞልቶ ከክፍል ሳይወጡ መረጃው ቀድሞ በአጥኚው ተሰብስበዋል፡፡ መረጃ እንዲሰጡ በናሙናነት ከተመረጡ 65 ተማሪዎች ውስጥ የጽሑፍ መጠይቁን 60 ተሳተፊ ተማሪዎች መረጃ የሰጡ ሲሆን ወ 2 ሴ 3 ድ 5 ተማሪዎች መረጃ አልሰጡም ምክንቱም በዕለቱ ወ 1 እና ሴ 2 አልተገኙም ወንድ 1 ሴት 1 ድ 2 ግን የመጠይቁን መመሪያ ተከትሎ አልሞሉም ይህ በመሆኑ በጥናቱ አልተከተቱም፡፡

### 3.3.2. የአንብቦ መረዳት ፈተና

የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለመለየት አገልግሎት ላይ የዋለ መረጃ መሰብሰቢያ አንዱ መሣሪያ ነው፡፡ የተማሪዎችን የክፍል ደረጃ መሠረት በማድረግ የተማሪዎችን የአንብቦ የመረዳት ችሎታ ለመለካት አንድ ምንባብ ከ9ኛ ክፍል አማርኛ ከተማሪው መማሪያ መጽሐፍ የተዘጋጀ ሲሆን አንድ ምንባብ ደግሞ አጠቃላይ አማርኛ ከ7ኛ-10ኛ ክፍል ከሚል አማርኛ አጋዥ መጽሐፍ ተዘገጅተው ለተጠኝ ተማሪዎች ቀርባዋል፡፡ ፈተናዎቹ ከተለያዩ መጽሐፎች የተወሰዱባት መነሻ ከአንድ መጽሐፍ ብቻ ከሚሆን ይልቅ የተለያየ ወይም ሁለት መጽሐፍት በመዘገጀቱ ጥሩ አስተማማኝነት ይኖረዋል በሚል ግምት ነው፡፡ ከሁለቱም ምንባቦች የወጣው ፈተናዎች የንባብ ፈተና ዘዴዎች መሠረት ያደረገ ሲሆን Alderson (2000,202) የንባብ ፈተና ተማሪዎች ከቀረበው ንባብ ውስን መረጃ ላይቶ እንዲያገኑ የንባቡን ዋና ሀሳብ፣ እንዲለዩ፣ የቃላት ትርጉም ከንባብ እንዲያገኑ የሚያስችሉ፣ የተማሪዎችን ችሎታ ያማከለ እንዲሁም ብርቱ ተሳትፎ የሚጠይቁ እና ግልጽ የሆነ ይዛት

ሊሆኑ እንደሚገባ ያስረዳሉ። በዚህ ሁኔታ 20 ጥያቄዎች የተዘጋጁ በመሆኑ የፈተናው ጥያቄዎችም የምንባቡን ዋናው መልዕክት አንብቦ መረዳት፣ከምንባቡ ውስጥ ቀጥተኛውንና ቀጥተኛ ያልሆነውን መረጃዎችን መለየትን፣በተጨማሪም አንድምታዊ ሀሳባችን የመረዳት ችሎታን የሚለኩ ሆነዋሉ። በመጀመሪያው የቀረበው ምንባብ በጥቅሉ 10 ጥያቄዎችን ይዟል ከእነዚህ ጥያቄዎች ውስጥ 7 የምርጫ ጥያቄዎች ሲሆን ቀሪዎቹ 3 ደግሞ አጭር መልስ ስጥ ጥያቄዎች ናቸው።

ሁለተኛው ምንባብ 10 ጥያቄዎችን የያዘ ሲሆን 5 እውነት ወይም ሀሰት 3 አዛምድ ጥያቄዎች ሲሆኑ 2 ጥያቄዎች ደግሞ አጭር መልስ ስጥ ናቸው። የአንብቦ መረዳት ፈተናም ልክ እንደ ጽሁፍ መጠይቁ ሁሉ በአማካሪ ከተገመገመ በኋላ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሚያስተምሩ መምህራን በሁለት እንዲገመገምና አስተያየት እንዲሳጥ ተደርጎዋል። ከላይ የተሰጡትን አስተያየቶች መነሻ በማድረግ መሻሻል ያለባቸውን ቃላትና ሀረጋት በማስወገድ እንደገና ተዘጋጅቷል። የአንብቦ መረዳት ፈተናው ልምድ ባለው በአንድ መምህርና በአጥኝው ለተሳታፊዎች እንዲሰጥ ተደርጎዋል። ለፈተነው የተፈቀደው ሰዓት 1፡00 ሲሆን ተማሪዎች ፈተናውን በትኩረትና በጥንቃቄ እንዲሰሩና የፈተናው ውጤትም ዋጋ እንደለው ተነግሯዋል። ይህም የሆነበት ምክንያቱም ተማሪዎች ፈተናውን በትኩረት እንዲሰሩ ስለሚያግዝ ነው። ሲጠቀላል ፈተናው በአጥኚው ከታረመ በኋላ ውጤት ተመዝግቦ ለትንተና ቀርቧል። በዚህ ሂደት ተማሪ በእያንደንዱ ፈተና ያገኘው ውጤት ከ10 በመስለት የሁለቱ ፈተናዎች ውጤት በአንድ ላይ ከ20% ከሆነ በኋላ ተተንትኗል።

## 3.4. የመረጃ አተናተን

በአንብቦ መረዳት ፈተና እና በጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች በመጠናዊ የመረጃ መተንተኛ ስልት እንዲተነተን ተደርጎዋል። ተማሪዎች በመማር ሂደት የሚጠቅሟቸውን ግለመር የመማር ዘዴዎች ምንድናቸው የሚሉትን ጥያቄዎችን ምላሽ ለመስጠት የነጠላ ናሙና ( t- test) ተግባራዊ ተደርጓዋል። ይህ ነጠላ ናሙና እንዲተገበር የሆነበት ምክንያት ተማሪዎች በመማር ሂደት የሚጠቀሟቸውን ግለመር የመማር ዘዴዎች ምንድናቸው የሚለውን ጥያቀ ምላሽ እንዲያገኝ ነው። ያለው (2009፣287)" የጥናቱ ተመረማሪው ከአንድ ጥናቱ አካላይ አባላት ውስጥ በዕጣ ንምና ዘዴ የተወሰኑትን በመምረጥ አንድ ጊዜ መረጃውን ከሰበሰበ በኋላ ያገኘውን መረጃ ቀደም ካለ አንድ የሚታውቅ ውጤት ጋር ለማወዳደር ሲፈልግ የሚጠቀመው ስልት ነው። በማለት ያስረዳሉ። ግለመር መማር ዘዴ፣ ተማሪዎች አንብቦ መረዳት ችሎታ መካከል ያለውን ዝምድና ለመፈተሽ (Pearson

product moment) የተዛምዶ መጠን መለኪያ ቀመር ተግባሪዊ ሆኖዋል፡፡
የፒርሰን ፕሮደክት ምሚንት የተዛምዶ ደረጃ ወይም መጠን መለኪያ ያተወሰደበት ሁኔታ ግለመር የመማር ዘዴዎች ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያለውን ዝምድና ለመፈተሽ ነው፡፡ ግብ ማስቀመጥ፣የመማር ፍላጎት፣የመማር ዘዴ እና ተማሪዎች ለግለመር መማር ዘዴ በአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ያለውን የማሳደግ ሚና ለመመርመር የህብረ ድህረታዊ ቀመር እንዲተገበር ተደርጎዋል፡፡ ይህ ቀመር ሂደት የተመረጠበት ምክንያት ያለው (2009፣361) "ህበረተዛምዶ በአንዱ ጥገኛ ተለዋዋጭና ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ነፃ ተለዋዋጮች መካከል ያለውን ግንኙነት የሚያሳይ ነው፡፡ አንድን ባህሪይ በአንድ ተለዋዋጭ ተመስርቶ ከማሳየት ወይም ከመተንበይ ይልቅ ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ተንበይ ተለዋዋጮች መጠቀም ተማረጭ ነው፡፡ጥናቱም የበለጠ ጠንካራ ያደረገዋል" ይላሉ፡፡

## 3.5. የመረጃ አሳባሰብ ሂደት

ይህንን ጥናታዊ ጽሁፍ አቅረብው በሥራው ከመግበቱ በፊት ስለ ጥናታዊ ሥራው ትም/ት ቤት ርዕሳነ መምህራን እንዲሁም ከ9ኛ ክፍል ከሚያስተምሩ አማርኛ ቋንቋ መምህራን ጋር ውይይት በማድረግ መረጃ በሚሰበሰብበት ወቀት እንዲተባበሩ ጥረት አድርገዋል፡፡
እንዲሁም የጥናት አቅራቢው በርዕሳን መምህራን ጋር በመሆን በምርምሩ ውስጥ የሚሳተፉ ተማሪዎችን ስለ ምርምር ተግባር ግንዛቤ እንዲኖር በማስረዳትና እንዲተባበሩ በማበረታተት በምርምር ሥራው እንደሚሰተፉ በማስረዳት መልካም ፍቃደኝነታቸውን አሳይቷዋል፡፡ ከትም/ት ቤቱ ርዕሳና መምህራን ጋር ወደ ተማሪዎች መማሪያ ክፍል በመሄድ አጥኚው የመጣበትን አላማ ለተማሪዎቹ ገለፃ ተደርጓዋል፡፡ በጥናቱ ሂደት መረጃዎችን በሚሳበሰብበት ጊዜ ችግሮች እንዳይኖሩ በጥናቱን ዋና አላማ በሚገልጽ መልኩ ለመረጃ ሰጪ ተማሪዎች ግንዛቤ ተሰጥቷዋል፡፡ በጽሑፍ መጠይቁና በአንብቦ መረዳት ፈተና ዙሪያ ግልጽ ያልሆነ ሀሳቦች ካሉ በመጠያቅ ግልፅ የሆነ ማበራሪዎች ተሰጥቷዋል፡፡ በትም/ት ቤቱ ውስጥ ከሚገኙ ሁለት 9ኛ ክፍል ተማሪዎች ወ 47 ሴ 38 ድ 85 መካከል በቀላል የዕጣ ንምና ዘዴ ወ 35 ሴ30 ድ 65 ተማሪዎችን ከተመረጡ በኃላ ፈተናውን እንድፈተኑ በማድረግ የተማሪዎች የፈተና ውጤት በስታትክስ ተተንትኗል፡፡

# ምዕራፍ አራት

## 4. የመረጃ ትንተናና የውጤት ማብራሪያ

### 4.1. የመረጃ ትንተና

ይህ ጥናት ዋና ተግባር የግለ መር መማር ዘዴ አማርኛ ቋንቋን አንብቦ ከመረዳት ችሎታ ጋር ያለውን ዝምድና መፈተሽ እንደሆነ በቀደሙት ምዕራፎች ለማሳየት ተሞክሯል። እንዲሁም በዚህ ምዕራፍ የጥናቱን ዋና ሀሳብ ከዳር ለማድረስ በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አማካይነት ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መጠናዊ መረጃዎች በመሰረታዊ ጥያቄዎች ስር እየተሰበሰቡ ተተንትኗል።

### 4.2. የመረጃ ሰጪ ተማሪዎች ዳራ ትንተና

በዚህ ጥናት ውስጥ የተሳታፊ ተማሪዎቹ አጠቃላይ ገጽታ የያዘ መረጃዎች የቀረቡ ሲሆን የተማሪዎች የክፍል ደረጃ ፣ መማሪያ ክፍል ፣ እንዲሁም ዕድሜና ፆታ የሚመለከቱ ጥያቄዎች ቀርባው ተተንትኗል ።

## ሰንጠረዥ 1 መረጃ ሰጪ ተማሪዎች ዳራ

| የትምህርት ቤት ስም | የክፍል ደረጃ | እድሜ | አጠቃላይ የተማሪ ብዛት | | | ለጥናቱ የተመረጡ ተማሪዎች ብዛት | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ |
| ጃንሶ እንጆጆ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት | 9ኛ | ከ15-17 | 47 | 38 | 85 | 35 | 30 | 65 |

ከላይ ከቀረበው ሰንጠረዥ የምንገነዘበው ጥናቱ የሚከሄድበት ትምህርት ቤት ጃርሶ ኦንጆ 2ኛደረጃ ትምህርት ቤት ሲሆን በአጠቃላይ 2015 ዓ.ም በ9ኛ ክፍል የሚማሩ ተማሪዎች ዕድሜያቸው ከ15 - 17 የሆነችው ወንድ = 47 ሴት= 38 ድ= 85 ተማሪዎች እንደሚማሩና ከእነዚህ ተማሪዎች ውስጥ ወንድ = 35 ሴት = 30 ድምር= 65 ለዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ የሚያስፈገውን መረጃ እንድሰጡ የተለዩ መሆኑን ማገነዘብ ይቻላል ።

## 4.3. ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳትን በመማር ሂደት የሚጠቀሟቸው የግለ መር መማር ዘዴን መፈተሽ

ተማሪዎች በሚማሩበት ጊዜ የሚጠቀሟቸው ግለ መር የመማር ዘዴ ምን ምን ናቸው? የሚለውን ጥያቄዎችን ምላሽ ለመስጠት የነጠላ ናሙና (t-test) ተግባራዊ ተዳርጎዋል፡፡ ነጠላ ናሙና (t-test) ተግባራዊ እንዲሆን የሆነበት ምክንያት ተማሪዎች በመማር አቅጣጫ የሚጠቀሙባቸውን ግለመር የመማር ዘዴዎች ምን ምን ናቸው የሚለውን ጥያቄዎች ለመመለስ ነው፡፡ ዋና ተግባር በቅድሚያ ጥናቱን በተመለከተ ለተማሪዎች ከቀረበው የፅሁፍ መጠይቅ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋን አንብቦ መረዳትን በመማር ሁኔታ ስለሚጠቀሟቸው የግለ መር መማር ዘዴዎች ከጽሁፍ ፈታና የተገኘው መረጃ በሚከተለው ሂደት ተተንትኗል፡፡

**ሠንጠረዥ2 : ተማሪዎች አንብቦ መረዳትን በመማር ሂደት የሚጠቀሟቸው የግለ መር መማር ዘዴዎች ፍተሻ በቲ - ቴስት**

| የግለ መር መማር ዘዴዎች | ናሙና | አማካይ | መደበኛ ልይይት | መደበኛ ስህተት አማካይ | ቲ-ቴስት | ጉልህነት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ግብ ማስቀመጥ | 60 | 26.417 | 2.403 | 0.310 | 85.134 | 0.016 |
| የመማር ፍላጎት | 60 | 26.966 | 2.149 | 0.280 | 96.192 | 0.016 |
| የመማር ዘዴ | 60 | 27.267 | 2.261 | 0.292 | 93.223 | 0.016 |

የነፃነት ደረጃ (Df )= 59 የሚጠበቅ አማካይ ውጤት = (Em) = 20

ሰንጠረዥ 2 ከሰፈረው መረጃ መረዳት እንደሚቻለው የተሳታፊዎች ግለመር የመማር ዘዴ አጠቃቀም አማካይ ውጤት ግብ መጣል 26.417 ፣ የመማር ፍላጎት 26.966 ፣ የመማር ዘዴ 27.267 ከሚጠበቀው አማካይ ውጤት (20) በልጦ ታይቷል፡፡ በአማካይ ውጤታቸው መሰረት የተማሪዎች የግለ መር የመማር ዘዴ አጠቃቀም አንዱ ከአንዱ የተቀራረበ ልዩነት አሳይቷል፡፡ በመሆኑም በአማካይ ውጤቱ መነሻነት በተማሪዎች ግለ መር የመማር ዘዴዎች አጠቃቀም መካከል ንፅፅር ሲደረግ ልዩነቱ ጠባብ ይምሰል እንጂ የዘዴ አጠቃቀማቸው ደረጃ ብንመለከት በመጀመሪያ ደረጃ የመማር ዘዴ ፣ በሁለተኛ ደረጃ የመማርፍላጎት እንዲሁም በሶስተ ኛደረጃ ግብ ማስቀመጥ በቅደም ተከተል ተመላክቷል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በመደበኛ ልይይቱ ላይም የሚታየው ልዩነት የሰፋ አይደለም፡፡ ይህ ልዩነት በስታትስቲክስ አስተማማኝ መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥ የሶስቱም ነፃ ተለዋዋጮች የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ዋጋ

ተሰልቷል። ውጤቱም ተሳታፊዎች ሁሉንም ግለመር የመማር ዘዴዎች በከፍተኛ ደረጃ እንደሚጠቀሙ አሳይቷል።

## 4.4. በግለ መር መማር ዘዴና በአንብቦ መረዳት ችሎታ መካከል ያለው ተዛምዶ ፍተሻ

የዚህ ጥናት ሁለተኛው መሪ ጥያቄ በግለመር የመማር ዘዴና በአንብቦ መረዳት ችሎታ መካከል ያለው ተዛምዶ ምን ይመስላል? የሚል ነው። በመሆኑም በግለ መር መማር ዘዴና በአንብቦ መረዳት ችሎታ መካከል ያለውን ዝምድና ለማወቅ የፒርሰን የተዛምዶ መጠን መለኪያ ቀመር በመጠቀም ተሰልቷል።ውጤቱም ከዚህ በታች ባለው ሠንጠረዥ ቀርቧል።

**ሠንጠረዥ3 :- የግለመር የመማር ዘዴና የአንብቦ መረዳትችሎታ ተዛምዶ በፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ ቀመር** (Pearson product moment)

| ተራ ቁጥር | ግለመር መማር ዘዴ | ግለመር መማር ዘዴዎች ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያላቸው ተዛምዶ | |
|---|---|---|---|
| | ተለዋዋጮች | የተዛምዶ መጠን | በ% |
| 1 | ግብ ማስቀመጥ | 0.592 | 35.046 |
| 2 | የመማር ፍላጎት | 0.721 | 52.012 |
| 3 | የመማር ዘዴ | 0.745 | 55.502 |

ናሙና= 60 ጉልህነት ($p<0.05$) df = 59

በሰንጠረዥ 3 እንደተመለከተው በፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ ቀመር መሰረት ሁሉም የግለመር የመማር ዘዴዎችከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር አዎንታዊ የሆነ ጉልህ ተዛምዶ አሳይተዋል። ምክንያቱም በአንብቦ መረዳት ችሎታና በግብ ማስቀመጥ መካከል ያለው ተዛምዶ ($r = 0.592$፣$p<0.05$) ጉልህ ሆኖ ተገኝቷል። ይህም በአንብቦ መረዳትና በግብ ማስቀመጥ መካከል አዎንታዊ የሆነ መካከለኛ ተዛምዶ መኖሩን ያመለክታል። በዚህም ሁለቱ ተለዋዋጮች አንብቦ መረዳት ችሎታና ግብ ማስቀመጥ 35.046 % ይጋራሉ። ይህ

ተማሪዎች ጥሩ ግብ እያስቀመጡ በሄዱ ቁጥር የአንብቦ መረዳት ችሎታቸው እየጨመረ እንደሚሄድ ያመለክታል ። በመማር ፍላጎትና በአንብቦ መረዳት ችሎታ መካከል ያለው ተዛምዶ ደግሞ (r =0.7212 ፣ p <0.05) ነው። ይህም በሁለቱም ተለዋዋጮች መካከል ከፍተኛ የሆነ አዎንታዊ ተዛምዶ እንደለ ስያመለክት ሁለቱም ተለዋወጮች 52.012 % ይጋራሉ። ይህም ተማሪዎች የመማር ፍላጎታቸው የጎላ እንደሆነ ያሳያል። በተመሳሳይ መልኩ በአንብቦ መረዳት ችሎታና በመማር ዘዴ መካከል(r=0.745 ፣ p<0.05) ከፍተኛ የሆነ አዎንታዊ ተዛምዶ አላቸው። አንብቦ የመረዳት ችሎታና የመማር ዘዴ የሚጋሩት 55.502 % ያህል ነው። ይህም በሁለቱ ተለዋዋጮች መካከል ያለውን የተዛምዶ መጠን ወይም የግንኙነት ደረጃ የሚያመለክት አዎንታዊ የሆነ ከፍተኛ ዝምድና ነው።

## 4.5. ግለመር መማር ዘዴዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታን የማሳደግ ድርሻ

የጥናቱ መሪ ጥየቄ ግለመር የመማር ዘዴዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታን የማሳደግ ድርሻ ምን ያህል ነው? የሚል ሲሆን ይህንን ጥያቄ ለመመለስ ህብረ ድህረታዊ ትንተና ተግባራዊ ተደርጓል። ይህንን አስመልክቶ ከተማሪዎች የተገኘው የፅሁፍ መጠይቅ መረጃ እንደሚከተለው ተተንትኗል።

**ሰንጠረዥ 4 ፡ ግለ መር የመማር ዘዴዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታን የማሳደግ ድርሻ የጉልህነት ደረጃ በህብረ ድህረታዊ ትንተና**

| ተላውጦዎች | የተጋርቶ መጠኝ (R square) | ድህረታዊ መጠኝ (B) | መደበኛ ስህተት (standard error) | መደበኛ ድህረታዊ መጠኝ (beta β) | የቲ - ዋጋ (t - test) | ጉልህነት Significan |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ግብ ማስቀመጥ | 0.552 | 2.329 | 0.907 | 0.299 | 2.567 | 0.016 |
| የመማር ፍላጎት | | 4.347 | 1.029 | 0.492 | 4.223 | 0.016 |
| የመማር ዘዴ | | 6.132 | 0.730 | 0.741 | 8.397 | 0.016 |

ሀ/ ጥገኛ ተላውጦ፦ (የአንብቦ መረዳት ችሎታ ውጤት)

ለ/ተንባይ ተላውጦ፦ (ግብ ማስቀመጥ ፣ የመማር ፍላጎት ፣ የመማር ዘዴ )

በሰንጠረዥ 4 እንደሚታየው የኅብረ ተዛምዶው የተጋርቶሽ መጠን($R^2$= 0.552) ወይም 30.47 % ነው። ህብረ ድህረታዊ ትንተና ውጤቱ እንደሚያመለክተው ግለመር የመማር ዘዴ በአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ያለው ድርሻ ($R^2$=0.552 F= 50.04 P<0.05) አስተማማኝ ነው። ይህም ሶስቱም ነፃ ተለዋዋጮች ማለትም ግብ ማስቀመጥ ፣ የመማር ፍላጎትና ፣ የመማር ዘዴ በጋራ በጥገኛ ተለዋዋጩ ማለትምበአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ የጎላ አስተዋጽኦ እንደላቸው ያመለክታል። በተጨማሪም ግለመር የመማር ዘዴዎች በአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ያላቸው ቀጥተኛ ተጽዕኖ ወይም ድርሻ ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ በመደበኛ ድህረታዊ መጣኝ(ß) ተሰልቶ የነፃ ተለዋዋጮቹ ድርሻ እንደሚከተለው ቀርቧል፦

ግብ ማስቀመጥ በተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ጉልህ የሆነ ድርሻ (ß=2.329, t=2.567 P<0.05) አለው። ይህም ተማሪዎች በትምህርታቸው ላይ የሚያቅዱት የአጭርና የረጅም ጊዜ ግብ የአንብቦ መረዳት ችሎታቸውን በማሳደግ በኩል ጉልህ የሆነ ድርሻ ያለው መሆኑን የሳያል። በተመሳሰይ ሁኔታ የመማር ፍላጎት የተማሪዎችን አንብቦ መረዳት ችሎታ ውጤት የማሳደግ ድርሻ ጉልህ መሆኑን (ß=4.347, t= 4.223 P<0.05) ያመለክታል።የመማር ዘዴ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ የማሳደግ ድርሻ በስታትስቲክስ (ß=6.132, t=8.397 p<0.05) ጉልህ ሆኖ ተገኝቷል።

በአጠቃላይ በድህረታዊ ትንተናው እንደተገለፀው የግለመር መማር ዘዴዎች የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ በማሳደግ አኳያ ያላቸው የተጋርቶ መጠን ($R^2$=0.552) ነው። ሶስቱም ነፃ ተለዋዋጮች በአንድነት ከጥገኛ ተለዋዋጩ ጋር 55.2% የልይይት መጠን ይጋራሉ። ይህ ማለት ለጥገኛ ተለዋዋጩ ባህሪ አስተዋጽኦ አድርጓል ወይም በጥገኘ ተለዋዋጩ ላይ ተፅዕኖ አሳድረዋል ማለትነው። ይህም የጎላ ውጤት ነው። ከዚህ በመነሳት ግብ ማስቀመጥ ፣ የመማር ፍላጎትና የመማር ዘዴ በጣምራ በአማርኛ ቋንቋ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ውጤት ላይ 55.2% ጉልህ ተፅዕኖ አሳድረዋል።

## 4.6. የውጤት ማብራሪያ

የጥናቱ ዋና ትኩረት በሀዲያ ዞን በምዕራብ በዳዋቾ ወረዳ ጃርሶ ኦንጆጆ ትምህርት ቤት "በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መማር ማስተማር ሂደት ውስጥ በተማሪዎች አንብቦ ከመረዳት ችሎታና በግለመር የመማር ዘዴ መካከል ያለውን ተዛምዶ መፈተሽ "ሲሆን ትኩረቱም በመፈተሽ መረጃዎች በስታቲስቲክስ ዘዴ ተተንትኗል።

በቅድሚያ ንዑስ ዓላማ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ተማሪዎች በመማር ሂደት የሚጠቅሟቸውን ግለመር የመማር ዘዴዎች መለየት ነው። ይኸውም በቅደመ ሙከራ ፈተና ውጤት መነሻ የንዑሳን የግለመር የመማር ዘዴዎች አስተማማኝነት በፓይሌት test ቀመር በተሰላው መሰረት አማካይ ውጤት የመማር ዘዴ 0.95 ግብ ማስቀመጥ 0.89 የመማር ፍላጎት 0.88 በቅደም የሚያሳይ ሲሆን በዲህረ ፈተና ደግሞ የመማር ዘዴ 27.267 የመማር ፍላጎት 26.966 ግብ ማስቀመጥ 26.417 ሊሆኑ ችሏል። እንዲሁም በአማካይ ውጤታቸው መነሻ የተማሪዎች የግለመር መማር ዘዴ የተጠጋገ ልዩነት እንደለው ያመለክታል። የግለመር መማር ዘዴዎች አጠቃቀም ሲነፃፀር የተቀራረበ ልዩነት ብኖረውም ውጤቱም ተሳታፊዉ ተማሪዎች ንዑሳን ግለመር የመማር ዘዴዎችን በውጤታቸው ቅደም ተከተል መሠረት ማጠቀመቸውን ያመለክታል።

የመጀመሪያው ንዑሳን ዓላማ ተማሪዎች በመማር ሂደት የማጠቅሟቸውን ግለመር መማር ዘዴዎችን መለየት ነው ። የጥናቱ ውጤት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በመማር አቅጣጫ ንዑሳን የግለመር መማር ዘዴዎችን በየደረጃ እንደሚጠቀሙ ያሳያል። ከዚህ የተነሳ ተማሪዎች በቅድሚያ የመማር ዘዴን፣በሁለተኛ የመማር ፍላጎት እንዲሁም በሶስተኛ ደረጃ ደግሞ ግብ ማስቀመጥ የሚጠቀሙ መሆኑን ያመለክታል። የተሳታፊዎቹ ግለ መር የመማር ዘዴ ደረጃ የተለያየበት ምክንያት ምናልባትም ተሳታፊዎች የመማር ዘዴዎችን ተግባራዊ አለማድረጋቸው ሊሆን ይችላል ወደ ሚል አንድምታ ልውስደን ይችላል። እንዲሁም የመደበኛ ልይይት ውጤት ግብ ማስቀመጥ 2.40 ፣የመማር ፍላጎት 2.14 የመማር ዘዴ 2.26 አንዱ ከአንድ የጥናቱ ተሳታፊዎች ውጤታቸው ምን ያህል በአማካይ እንደምርቁ የሚያሳይ ሲሆን የሚታየው ልዩነት በጣም የረቃ አይደለም ። በመሆኑም ከፍተኛ መደበኛ ልይይት የተሳታፊዎችን የባህር ልዩነት ሲያመለክት ፣ አነስተኛ መደበኛ ልይይት ደግሞ የባህር መመሳሰልን ያመለክታል ያለው (2009)። እንዲሁም ይህ የተያው ልዩነት በስታትስቲክስ አስተማማኝ መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥ ከአንድ የጥናቱ አካለይ አባላት መካከል የተወሰኑትን በመምረጥ አንድ ጊዜ ከተሰበሰበው መረጃ ያገኛውን ቀድሞ ከአንድ ከሚታወቅ ውጤት ጋር የሶስቱም ነጻ ተለዋዋጮች የነጠላ ናሙና የቲ-ቴስት ዋጋ ተሰልቷል። የውጤት በጥናቱ ውጤት ሂደት ተሳታፊዎች ጎን ለጎን ሁሉንም የግለመር መማር ዘዴዎችን የሚጠቀሙ ሲሆኑ ነገር ግን ምርጫቸው እውን የሚያደርግ የመማር ማስተማር አቅጣጫና ድጋፍ ካልተመቻቸላቸው ግለመር የመማር ዘዴዎችን በተመሳሰይነት ደረጃ እንዲጠቀሙ መጠበቅ አስቸጋሪ ይሆናል። ከዚህ ሁኔታ ጋርተያይዞ (Conley,1992) ማንኛውም መምህር በክፍል ውስጥ አንብቦ መረዳትን ሲያስተምር በተለያዩ ምክንቶች

ትምህርቱን የማይማሩ በርካታ ተማሪዎች እንደምኖሩና የእነዚህ ተማሪዎች ችግር ተገቢ የሆነ የመማር ዘዴዎችን ካለመጠቀም ጋር እንደሚያያዝ ያስረዳሉ፡፡ Zimmermen (2002) በበኩላቸው ተማሪዎች በሚማሩበት ወቅት ሁሉንም የግለመር መማር ዘዴዎችን በእኩል እንድገለገሉ የመማር ማስተማር ስራ የዘዴ አጠቃቀምን የመካለ መሆን እንደለበት ይጠቁመሉ፡፡

ሁለተኛው የጥናቱ ንዑስዓላማ በግለመር የመማር ዘዴና በአንብቦ መረዳት ችሎታ መካከል ያለው ተዛምዶ ምን እንደሚመስል መፈተሽ ነው፡፡ በዚህ መሰረት የጥናቱ ውጤት የግለመር መማር ዘዴዎች ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር በስታትስቲክስ በፒርሰን የተዛምዶ መጠን መላኪያ መወሰኛ ቀመር በመጠቀም ተሰልቷል ምክንያቱም በግብ ማስቀመጥና አንብቦ መረዳት ችሎታ መካከል ያለው ተዛምዶ ወይም የተጋርቶሽ መጠን (r=0592, P<0.05) ጉልህ ሆኖ ሲገኝ በግብ የሁለቱ ተለዋዋጮች ከመቶ 35.046% እንደሚጋሩ አሳይቷል፡፡ ይህም ተማሪዎች ግብ እያስቀመጡ በሄዱ ቁጥር የአንብቦ መረዳት ችሎታ እየጨመረ እንደሚሄድ ሲያመላክት በመካከላቸውም አዎንታዊ የሆነ ተዛምዶ መኖሩን ገልጾዋል፡፡ ከመማር ፍላጎትና በአንብቦ መረዳት ችሎታ ያለው ተዛምዶ (r=0.72.1፣ P<0.05) የጎላ እንደሆነ ሲያመላክት ተለዋዋጮቹ ከመቶ (52.012)% በመጋራት በመካከላቸው ከፍተኛ የሆነ አዎንታዊ ተዛምዶ መኖሩን ያሳያል፡፡ እንዲሁም በአንብቦ መረዳትና በመማር ዘዴ መካከል (r=0.745፣ P<0.05) ከፍተኛ የሆነ ተዛምዶ ሲኖረው ሁለቱ ተለዋዋጮች ከመቶ 55.502% በመጋራት የተዛምዶ መጠን በመካከላቸው አዎንታዊ የሆነ ከፍተኛ ዝምድና እንዳለው ያመላክታል፡፡ ይህም በሁለት ተለዋዋጮች መካከል የሚኖረው ተዛምዶ በተለያዩ አቅጣጫ የሚገለጽ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ የተዛምዶ አቅጣጫ በሁለቱ ተዛማጅ ተለዋዋጮች መካከል ያለው የግንኙነት መልክ ሲሆን ከፍ ብሎ የተገለጸው የተዛምዶ አቅጣጫ አዎንታዊ ተዛምዶ እንዲለው ያሳያል፡፡ በመሆኑም የተዛምዶ መለኪያ ዘዴዎችን በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ መጠናዊ ተለዋዋጮች፣ መካከል ያለውን ግንኙነት መጠን ለመወሰን ይረዳል ያለው (2009፣324)፡፡

በግለመር የመማር ዘዴና በአንብቦ መረዳት ችሎታ መካከል በተደረገው የተዛምዶ ትንተና የተገኘው ውጤት ከመካከለኛ እስከ ከፍተኛ የሆነ አዎንታዊ ተዛምዶ እንዳላቸው አመልክተዋል፡፡ ይህ ደግሞEric (2011) ከጠኑት የጥናት ግኝት ጋር ተደጋጋፊነት ያለው ሲሆን የተሻለየአንብቦ መረዳት ችሎታ ያላቸው ተማሪዎች የተሻለ የዘዴ ተጠቃሚ እንደሆኑና በተቃራኒው ዝቅተኛ የዘዴ አጠቃቀም ያላቸው ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታቸውም ዝቅተኛ እንደሆነ ጥናቶቹ አመልክቷል፡፡

ሶስተኛው የጥናቱ ንዑስ ዓላማ ግለመር የመማር ዘዴ የአንብቦ መረዳት ችሎታን የማሳደግ ድርሻው ምን ያህል እንደሆነ ማመልከት ነው፡፡ እንዲሁም ይህ ጥያቄ ምላሽ ለመገኛት አጥኚዉ የህብራ ድህረታዊ መጠን መላኪያ ቀመረ በመጠቀም ተሰልቷል፡፡ ምክንያቱም አንድ ጥገኛና ከአንድ በላይ ነፃ ተለዋዋጮች ከተጠቀመ ደግሞ ህብረ ድህረታዊ ትንተና ሲሆን በድህረታዊ ትንተናው እንዳተገለጸው የግለመር መማር ዘዴዎች የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ በማሳደግ አኳያ ያላቸው የተ.ጋርቶ መጠን (R =0.552)ነው ፡፡ የሶስቱም ነፃ ተለዋዋጮች በአንድነት ከጥገኛ ተለዋዋጩ ጋር 55.2% የልይይት መጠን ይጋራሉ ፡፡ይህ ሂደት ለጥገኛ ተለዋዋጩ ባህሪ አስተዋጾ አድርጓል ወይም በጥገኛ ተለዋዋጩ ላይ ተፅዕኖ አሳድረዋል፡፡ ከዚህ በመነሳት ሶስቱም ተለዋዋጮች በአንድነት የአንብቦ መረዳት ችሎታ ውጤት ላይ 55.2%ጉልህ ተፅዕኖ አሳድረዋል፡፡ አንድን ባህሪ በአንድ ተለዋዋጭ ተመስርቶ ከመተንባይ ይልቅ ሁለትና ከዚያ በላይ የሆነ ተንባይ ተለዋዋጮችን መጠቀም ተመረጭ ነው ጥናቱን የበለጠ ጣንካረ ያደርገዋል ያለው (2009፣361) ፡፡ በዚህ መሰረት ውጤቱ የግለመር መማር ዘዴዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታን የማሳደግ ድርሻቸው ከፍተኛ እንደሆነ አሳይቷል፡፡ ግብ ማስቀመጥ ፣ የመማር ፍላጎት ፣ የመማር ዘዴ የአንብቦ የመረዳት ችሎታ በማሳደግ አኳያ ከፍተኛ ድርሻ አላቸው፡፡ ለያብቻ ሲታይ የመማር ዘዴ፣ የመማር ፍላጎትና ግብ ማስቀመጥ እንደ ቅደም ተከተለቸው ለአንብቦ መረዳት ችሎታ መጨመር ወይም ማዳበር የተሻለው አስተዋፅኦ አሏቸው፡፡ ይህ ውጤት ደግሞ ከAburhman&Nasrha (2012) ከጠኑት የጥናት ውጤት ጋር የሚቀራረብ ነው፡፡

በአጠቃላይ ይህ ጥናት ተማሪዎች በመማር ሁኔታ በፈተናና በጽሁፍ መጠይቅ በተገኘው ውጤት በስታትስክስ ትንተና መሠረት የመማር ዘዴ፣የመማር ፍላጎትና ግብ ማስቀመጥ በቅደም ተከተለቸው የግለመር የመማር ዘዴዎች በጉልህነት እንደሚጠቀሙ ያመለክታል፡፡ ከዚሁ በተጨማሪም ሌላ ይህ ጥናት በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በተማሪዎች የግለመር መማር ዘዴ አጠቃቀም መካከል የተቀራረበ ልዩነት መኖሩንም ያመለክታል፡፡ እንዲሁም ተማሪዎች ግብ ከማስቀመጥና ፣ ከመማርፍላጎት በተሻለ ሁኔታ የመማር ዘዴን መጠቀም መቻለቸውን የተገኘው ውጤት ያመለክታል፡፡ በዚህ ሁኔታ በግለመር የመማር ዘዴና በአንብቦ ከመረዳት ችሎታ መካከል ጉልህ ተዛምዶ እንዳለው የውጤት ትንተናው ያመለክታል፡፡ ግለመር የመማር ዘዴ የአንብቦ ከመረዳት ችሎታን የማሳደግ ድርሻው የተሻለው እንደሆነ ከቀረበው ትንተና ውጤት መረዳት ይቻላል ፡፡ እንዲሁም መማር በመማር ዘዴዎች ታግዞ ሲተገባር ውጤቱ የተሻለ ይሆናል፡፡ግለመር የመማር ዘዴ

በትምህርት የሚያገኛውን ዕውቀት በአግበቡ የመቀበል፣የማዘመድ፣ ከግለቸው ተግባር ጋር የመያዝና የማስታወስ ተግባር ሲለሆነ በተለየያ አቅጣጫ የተገኛውን መረጃ በማጥናት በአስተሳሰበቸው ወይም በአእምሯቸው ሲያስፈልገው በማስታወስ ለመማር የሚጠቀሙበት ሂደት በመሆኑም የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የሚያስተምሩ መምህራን የሚያስተምሩትን ትምህርት በሚያቅዱበትም በሚተገብሩበትም ሆነ እንዲሁም ሲገመግሙ የተማሪዎችን የግለመር የመማር ዘዴ አተገባበር ከግምት ውስጥ ማስገባት እንዳለባቸው የጥናቱ ውጤት አቅጣጫ ያመለክታል ።

# ምዕራፍ አምስት

## 5. ማጠቃለያና አስተያየት

### 5.1. ማጠቃለያ

የጥናቱ አቢይ አላማ በግለመር መማር ዘዴ አማርኛ ቋንቋን አንብቦ ከመረዳት ችሎታ መካከል ያለውን ተዛምዶ መፈተሽ ነው፡፡ በዚህ መሰረት በጥናቱ በቀዳሚነት መልስ እንዲገኝባቸው የተነሱት መሰረታዊ ጥያቄዎች የሚከተሉት ነበሩ፡፡

1. 1.የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች አንብቦ መረዳትን በሚማሩበት ጊዜ የሚጠቀሟቸው የግለስ መር መማር ዘዴዎች የትኞዎች ናቸው?
2. በግለመር የመማር ዘዴና በአንብቦ መረዳት ችሎታ መካከል ያለው ተዛምዶ ምን ይመስላል?
3. ግለመር የመማር ዘዴ አንብቦ የመረዳት ችሎታን የማሳደግ ድርሻው ምን ያህል ነው?

የጥናቱን መነሻ ጥያቄዎች ለመመለስ ይቻል ዘንድ  የጽሁፍ መጠይቅ ፈተና ለመረጃ መሰብሰቢያ ተግባራዊነት ሆኖዋል፡፡  የጥናቱ ተሳታፊዎች በሀዲያ ዞን በምዕራብ ባዳዋቾ ወረዳ ጃርሶ ኦንጆጆ 2ኛ ደረጃ በ2015 ዓ.ም. በ9ኛ ክፍል ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ያሉ ተማሪዎች ናቸው፡፡ በዚህ የክፍል ደረጃ ከሚማሩ ወንድ 47 ሴት 38 በድምር 85 ተማሪዎች ትምህርታቸውን ይከታተላሉ፡፡ በትምህርት ቤቱ ከሚማሩ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ውስጥ በዕድል ሰጭ የንምና ዘዴ ውስጥ የተከታታውን ቀላል የዕጣ ንምና ዘዴ በመጠቀም ወ 35 ሴ 30ድምር 65 ተማሪዎች ዕጣ በማውጣት ተማሪዎች በጥናቱ መሳታፊ እንዲችሉ ተመርጦዋል፡፡ የጥናቱ ዋነኛው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ የጽሁፍ መጠይቅ እና የአንብቦ መረዳት  ፈተና ሲሆኑ የተማሪዎቹ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ውጤትም በፈተና አማካይነት ተሰብስቦ ስታትስቲካዊ የቅመራ ዘዴዎችን በመጠቀም ተተንትነዋል፡፡

የጥናቱን ዋና ጥያቄዎች መነሻ በማድረግ ጥናቱን በሚከተለው አቅጣጫ  ማጠቃለያ ተዳርጎበታል፦

የመጀመሪያው ዋና ጥያቄዎች የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች አንብቦ መረዳትን በሚማሩበት ጊዜ የሚጠቀሟቸው የግለ መር መማር ዘዴዎች የትኞዎች ናቸው? የሚል ሲሆን በውጤት ትንተናው መሰረትም ተሳታፊዎች በመማር ሂደት ሁሉንም የግለመር መማር ዘዴዎች እንደሚጠቀሙ በስታትስቲክስ ጉልህ ውጤት ተገኝቷል፡፡ በተጨማሪም የጥናቱ ተሳታፊዎች

የሚጠቀሙባቸው የግለ መር መማር ዘዴዎች ወይም ንዑሳን ግለመር መማር ዘዴ ግብ ማስቀመጥ ፣ የመማር ፍላጎትና የመማር ዘዴ አጠቃቀም በተደረገው ንፅፅር በእስታትስቲክስ (P<0.05) ጉልህ ልዩነት አሳይቷል ፡፡

ሁለተኛው መሪ ጥያቄ በግለመር የመማር ዘዴና በአንብቦ መረዳት ችሎታ መካከል ያለው ተዛምዶቸው ምን ይመስላል? የሚል ሲሆን የግለመር መማር ዘዴዎች ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር አዎንታዊ የሆነ ተዛምዶ እንደላቸው የጥናቱ ውጤት አመልክቷል፡፡ የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ከግብ ማስቀመጥ ፣ከመማር ፍላጎትና ከመማር ዘዴ ጋር የጎላ አዎንታዊ ግንኙነት እንደላቸው የጥናቱ ውጤት ያመለክታል ፡፡ ለተዛምዶውም ከፍተኛውን ቦታ በመያዝ የተሻለውን ድርሻ የሳያው የጥናቱ ተሳታፊዎች የመማር ዘዴ ነው፡፡

ሶስተኛ መሪ ጥያቄ ግለመር የመማር ዘዴ አንብቦ የመረዳት ችሎታን የማሳደግ ድርሻው ምን ያህል እንደሆነ ? የሚል ሲሆን ውጤቱም የግለመር መማር ዘዴዎች አንብቦ መረዳት ችሎታን የማሳደግ ድርሻቸው ከፍተኛ እንደሆነ በትንተናዉ ውጤት ተመለክቷ፡፡ በልዩነት ሲታይ ደግሞ የመማር ዘዴ ግብ ከማስቀመጥና ከመማር ፍላጎት የተሻለ የማሳደግ ድርሻ ወይም ተግባር እንዳለው ከጥናቱ ውጤት ለመረዳት ተችሏል፡፡

## 5.2. አስተያየት

በዚህ ጥናት ውስጥ የተደረሰባቸውን ውጤቶች ተግባራዊ እንዲሆን ወይም ለመከናወን እንዲቻል የሚከተሉት አስተያየቶች ተመለክቷል፡፡

1. የአማርኛ ቋንቋን የሚያስተምሩት መምህራን የአንብቦ መረዳት ትምህርት ሲያዝገጁና ሲገመግሙ የተማሪዎችን ዝንባሌና የመማር ዘዴዎችን ከግምት ውስጥ ቢያስገቡ፣
2. በዚህ ጥናቱ ውስጥ የተገኘውን መረጃ እንዳሚያመለክተው የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የግለመር መማር ዘዴዎችን የመጠቀም ሂደት የተሻለ በመሆኑ ይህንን ችሎታቸውን በተግባር እንዲጠቀሙበት ሚመለከታቸው የአማርኛ ቋንቋ የሚያስተምሩ መምህራንና የትምህርት ባለሙያ አካላት ቢደግፉቸው፣
3. ይህ ጥናት በተማሪዎች የግለመር የመማር ዘዴና አንብቦ ከመረዳት ችሎታ መካከል አዎንታዊ ተዛምዶ መኖሩን ገልጾዋል፡፡ እንዲሁም ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ስርአት ትምህርቱን ሲያዘጋጁ የቋንቋ መማሪያና ማስተማሪያ መፅሐፍት በማዘጋጃት የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማሳደግ የዘዴውን ስልጠና እንደ አንድ ተግባር ቢያቀሪቡ፣

4. ግለመር የመማር ዘዴዎች  የተለያየ  ሲሆኑ በዚህ ጥናት አላማ የደረገው ግብ ማስቀመጥ ፣የመማር ፍላጎትና የመማር ዘዴ ሲሆኑ በሂደቱ ጥናት ማካሄድ የሚፈልጉ ተመራማሪዎች በዚህ ጥናት ባልተጨማሩ  በሌሎች የግለመር መማር ዘዴ ንዑሳን ክፍሎች ማለትም  ራስን መዘጋጃት፣ የግልጥራትና በትምህርት  ያተገኛውን ውጤት በመገምገም የተለያዩ ጥናት ቢያካሂዱ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለማሳደግ ያለው ድጋፍ የተሻለ ልሆን ይችላል። በአጠቃላይ  ደግሞ የአማርኛ ቋንቋን  የሚማሩ ተማሪዎች እንዲሁም የሚየሰተምሩ መምህራንን ጨምሮ  ለግለመር መማር  ዘዴ ያለው ግንዘቤ የተሻለና  አንብቦ መረዳት የግል ተግባር ስለሆነ  በግለመር መማር ዘዴዎች ላይ ተዳግፎ ተግባራዊ  ቢሆንና ቢያሻሽል የተማሪዎች የመማር ውጤት የተሻለ ለውጥ  እንዲኖረው  ይረዳዋል።

## 5.3. መደምደሚያ

በዚህ ጥናት ዋና ዓላማ "ግለመር መማር ዘዴ አማርኛ ቋንቋን አንብቦ ከመረዳት ችሎታ መካከል ያለውን ተዛምዶ መፈተሽ " የሚል ነበር ዓለማውንም ለማሳካት የተለያዩ ተግባራት ተካሄደው በተገኘው ውጤትና በተገለጸው ማብራሪያ መሰረት ከሚከተሉት መደምደሚያዎች ላይ ተደርሷል።

1. በቅድሚያ ንዑሳን ዓላማ  በአማርኛ ቋንቋ  ትም/ት ተማሪዎች  በመማር ሂደት የሚጠቀሚባቸውን የግለመር መማር  ዘዴዎች ተለይተው ተወቁዋል ። ይኸውም በቅድመ ሙካራ ፈተና ውጤት መነሻ የንዑሳን የግለመር የመማር ዘዴዎች አስተማማኝነት በተሰጠው በፓይሌት  test  ቀመር በተሳለው  መሰረት በአማካይ ውጤታቸው መሰረት በቅድመ ውጤት አጠቃቀማቸው የታያበት ነው ። ተማሪዎች በድህረ ፈተና የግለመር መማር ዘዴ ውጤት የሶስቱም ነፃ ተለዋዋጮች የተቀራራብ ውጤት ቢኖረውም በቅድመ ሙካራ ፈተና እንዳታያወም በቅደም ተከተለቸው የመማር ዘዴ ፣የመማር ፍላጎት እና ግብ ማስቀመጥ በደረጃቸው ተማሪዎች እንደሚጠቀሙ ያሳያል።
2. ተማሪዎች በግለ መር መማር ዘዴ ውስጥ የተከተቱትን ንዑሳን የግለመር መማር ዘዴ ከአንብቦ መረደት  ችሎታ ያለው ተዛምዶ ተማሪዎች በተለኩ የአንብቦ መረዳት ፈተናና  የጽሁፍ መጠይቅ ፈተና የተማሪዎች የግለ መር መማር ዘዴና የአንብቦ መረዳት ችሎታ መካከል ባሳያው በስታትስቲክስ ትንተና የተዛምዶ መጠናቸውም አዎንታዊ የሆነ ተዛምዶ እንደላቸው ተይቷዋል።

3. የግለመር መማር ዘዴዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታን የማሳደግ ድርሻ በግለመር መማርና በአንብቦ መረዳት ችሎታን በመካከለቸው ላይ በተደረገው ፈተናና የጽሁፍ መጠይቅ ፈተና ውጤት መሰረት በተማሪዎች የግለመር መማር ዘዴ የአንብቦ ከመረዳት ችሎታን በተተነተናው ውጤት የማሳደግ ድርሻ ከፍተኛ እንደሆነ ተይቷዋል፡፡

# ዋቢ ጽሑፎች


ማረው ዓለሙ ፡፡ (1990)፡፡ የመማር ምርጫና የትምህርት ውጤት ተዛምዶ፡፡ The Ethiopian journal of Education.

ማስተዋል ውበቱ ፡፡ (1989)፡፡ "የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች በአማርኛ የአንብቦ መረዳት ችሎታ በአዲስ አባበ በሚገኙ በአራት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአስራ አንደኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ጥናት፡፡" ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፣አዲስ አበባ ያልታተመ፡፡

ሰለሞን ሀለፎም፡፡ (1994)፡፡ ቋንቋን የማስተማር ስነ-ዘዴ፡፡ አዲስ አባበ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)

ባንቺ አምላክ ፈጠነ፡፡ (2013)" አእምሯዊ የመማር ብልሃቶችን በግልፅ ማስተማር አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማጎልበት ያለው አስተዋፅኦ" ለአርትስ ማስተርስ ድግሪ ማሟየነት የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ፣አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፡፡ (ያልታተመ)

ብርሃኑ ገ/ጻድቅ ፡፡ 2010፡፡ አጠቃላይ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መመሪያ ከ7ኛ-10ኛ ክፍል ፡፡ በረከት ማተሚያ ኃላ/የተ/የግ/ማ፡፡

ተስፋዬ ሸዋዬ፡፡ (1986)፡፡ አንብቦ መረዳትና የመጽፍ ችሎታን ማዳበር፡፡ አዲስ አበባ ት.መ.ማ.ማ.ድ፡፡

ታደሰ ዳርገው፣ማረው አለሙና ሙሉጌታ ተካ 2010"የራስ መር መማር ብልሀቶች አንብቦ የመረዳት ችሎታና ብልሀቶች አጠቃቀምን የማሳደግ ሚና በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት" በጎንደር ከተማ አስተዳደር በልዑል አለማየሁ ቴዎድሮስ 1ኛ ደረጃ ት/ ቤት በ2010 ዓ.ም በ7ኛ ክፍል ትምህርታቸውን በሚመሩ ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ጥናት ፣ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ፣Vol No.1 https/www.Research Gate.Net/publication 344306022.

ትምህርት ሚኒስትር ፡፡(2007)፡፡ አማርኛ የተማሪ መጽሐፍ 9ኛ፡፡አዲስ አበባ ፣ኩራዝ ኢንተርናሽናል አሳታሚ ኃ/የተ/የግ/ማህበር

አለም እሸቱ ፡፡ (1997)፡፡ መሠረታዊ የምርምርና የዘገባ አፃፃፍ፡፡ አዲስ አባበ፣ commercial printing Enterprise.

አስቴር አስራት፡፡ (2010)፡፡ "የቤተሰብ ዳራ የአንብቦ መረዳት ችሎታን የመተንበይ ድርሻ" ለአርትስ ማስተርስ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ፅሁፍ፤ አዲስ አበባ

ዩኒቨርሲቲ ፡፡ ያልታተመ፡፡

ያለው እንዳወቀ፡፡ (2009)፡፡ የምርምር መስረታዊ መርሆዎችና አተገባበር፡፡ አዲስ አበባ፣ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ፋሲካ ውበቱና አገኘሁ ተስፋ፡፡ (2008)፡፡ "በትብብር መማር አንብቦ በመረዳት ችሎታና ፍላጎት ላይ ያለውን ሚና መፈተሽ" በአማረ ክልል በሰሜን ጎንደር ዞን በጎንደር ከተማ በፋሲላደስ መሳናዶ ት/ቤት በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ያካሄዱ ጥናት፣ERJSSH S(2). Decmeber 2018 orginal ariticle፣ ጎንደር ዩኒቨርስቲ፡፡

Abdurahiman,A.& Nasrah,M. (2012). Self Regulated Learnimng strategy as precdictor of Reading comprhantion among student of English as Foreign language.

Abas and et'al.(2016). A self Regulated learning Strategies as predictors of reading comprehension' Iranian EFL learners.Journal of Recent research in English language studies Vol.3 No.2,pp.21-34,2016

Alderson, Charies. (2000). Assessing Reading.Cambirdge: Cambirdge Unversity press.

Aljuaid, H.& thallab,K. 2015. Language learing strategies used by agroup of saudi Arabian learners. School of education and professionalstudies: https: /doi, org/ 10259041912/2905

Bandura ,A (1986). Social Foundations of thought and Action: A Social Cognitive Theroy .Englewood Cliffs,NJ:prentice Hall.

---------------- (2011).Social cognitive theory agnatic perspective. Annual review of psychology. Retrived from Chicago jornal.http:// www.jstor. org/stable/ 10228.

Block.c.c.(1997). Teaching the language arts: expanding thinking through student centered instruction. Boston; allyan& Bacon.

Brown, H.D.(1994). principles of language learning & teaching: Cambridge. Cambridge prentice hall.

Chamot,A.U. and kupper, L. (1989).Learning strategies in foeign language instruction. Foreign language Annals, N22,pp 13-24.

Cole,G .(1996).Teaching principle & practice. (2nd ed) Newyork: prentice Hall

intemationak (uk) Ltd.
Conely, M.(1992). Content reading instruction; communication approach.New Yok. Mcgraw hill. inc
Davies,F. (1995). Introducing ReadingCombridge :university press.
Ellis,R. (1994).Understanding 2nd language AcquisitionOxford: oxford university press.
Eric, C.C.K. (2011). Change the role of self regulated learing in Enhancipe rformance. The Hang kong institute of education: Hang kong, the intemational joumal of research and Review volume 6 issue 1. March 2011.1.
Evangelisto,T.(2002).Constructivist approaches to Theaching and learning. California.educational Administration and Secondary Education.The college of New Jersey(Ewi,NJ, USA)
Farrant, J.S.(1980.30) principles and practice of Education .Great Britain: longman.
Gardner .R.(1985).Social psychology and Second Motivation. Great Britani Edward Am old Ltd
Greenwood, j.(1981). Compreshension & ReadingIn the teaching of English as an international language: practical guide. G abbot and p. wagard (eds) pp81-11
Grahant.R.J .(1967)“content reading and the recreation mening ›› in ELT.jonral 76/2.98.99
Grellet,F .(1981).Developing Reading skills Combridge University press.
Lencion, G.M.(2021).The Effects of Explicit Reading strategy Instruction and Cooperative learning on Reading Comprehension in Fourth Grade Students. San francisco :university of San francisco .USF scholarship Repository.
Harmar, j. (2001).The practice of English language Teaching: New York longman.

Kavale, k. (1979)."Selecting and evaluating reading tests ." in Reading tests and teachers: A practical guide. Schreir(ed.),pp.9-32.

Mohammed, A.& salmani ,N. (2012). Self regulated learning (SRL): Emergence of the RSRLM model'intemational jornal of language Studies(IJLS).Vol6(3),2012(Pp1-16).

Najva, S . (2015). The effect of teaching self regulated learning strategies on EFL students'reading comprehension.college of foreign languages and literature,science and research ,vol-,6 pp1343-134,academy publication.

Oxford, R. L,(1990). language Learning Strategies.What Every Teacher should know .New York: New bury House

Pintrich, P.R. (1995). Understanding self regulatedlearning: New Direction for Teaching & Learing, No 63, fall 199, jossey bass publisher.

Rowell, C.G.,and palmer,B.C.(2007).Congnitive and Constructivist Strategies for teaching about language and for providing Reading and writing lnstruciton.Forum onpubic policy pp 1-30

Richards, j., and Lockhart.C. (1996). Relfective teachingin second language class rooms Cambridge: combridge unvirsity press.

Stern ,H.H.(1983) Fundamental Conceepts of language teaching Oxford university press.

Williams ,M and (1990).psychology for language teachers. A sociapl Constructivist Approach Cambridge.Cambridge university press.

Zimmerman , B .(1990) Self -Regulated learning and Academic Achievement:An Overview http://www.tandfonline.com/action /Journal lnformation? Journal Code =hed20 Download by: [vancouver Island university]Date:02,published online:08 Jun 2010

--------------------- (2002) .becoming aself regulated learner. Unversiti of New York: Retraived from WWW. Research gate net (profile) barry Zimmeman publicati.

# አባሪዎች

## አባሪ አንድ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂዩማኒቲስ:የቋንቋዎችጥናት የጆርናሊዝምና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ሥነ-ጽሁፍናፎክሎር ክፍል ትምህርት የድህረ-ምረቃ መርሃ ግብር "በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የግለ መር መማር ዘዴ አንብቦ ከመረዳት ችሎታ ጋር ያለው ተዛምዶ መፈተሽ" በሚል ርዕስ ለሚካሄደው ጥናት አስፈላጊውን መረጃ ለመሰብሰቢ የተዘገጀና በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የሚሞለ የፅሁፍ መጠይቅ ፡፡

**ውድ ተማሪዎች ፦**

## የፅሁፍ መጠይቅ

ይህ የፅሁፍ መጠይቅ "በአማርኛ ትምህርት የግለመር መማር ዘዴ ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያላው ተዛምዶ መፈተሽ" በሚል ርዕስ ለሚከናውን የምርምር ስራ መረጃ ለማግኘት የተዘገጃነው፡፡ በመሆኑም ጥናቱ ከግብ ይደርስ ዘንድ የእናንተ ቀናና ትክክለኛ ምላሽ ለጥናቱ ስኬት አሰፈለጊ ስለሆነ ለቀረበላችሁ ጥያቄ ትክክለኛ ምላሽ እንዲትሰጡ በትህትና እየጠያኩ ጊዜያችሁን ሰጥተቸሁ መጠይቁን ለመሙላት ስለተባባረችሁኝ በቅድሚያ አመሰግናለሁኝ፡፡

**ማሳሰቢያ ፦**

- ★ ስም አይጻፍም: የክፍል ደረጃ ፣ መማሪያ ክፍልና መለያ ቁጥር ይጻፈል ፡፡
- ★ ጥናቱ የግሉን ምላሽ ስለሚጠይቅ የጋራ ስራ አያስፈልግም፡፡
- ★ ፆታ፦ወ ..... ሴ ........ዕድሜ.............የአፍመፍቻቋንቋቸው ................................

**አጠቃላይ መመሪያ ፦**

- ✓ የመጠይቁ አሞላል ከጥያቄዎቹ ፊት ለፊት ካተሰጡት ከ 1 እስከ 4 ካሉት አማራጮች መካከል አንዱን ብቻ መርጦ በመክባብ ነው ፡፡
- ✓ በመጠይቁ በጥያቄዎቹ ፊት ለፊት ከ 1 እስካ 4 ያሉት ቁጥሮች ቀጥሎ ያሉትን የውሳኔ ሀሳቦች የያዙ ናቸው ፡፡

1. በጣም አልስማማም 2 . አልስማማም
3. እማማለሁ 4 . በጣም እስማማለሁ

ከዚህ ቀጥሎ የቀረብኳቸው ሀሳቦች ንኡሳን የግለመር መማር ዘዴምን እንደሚማስል የተመለከቱ ናቸው ። ከተሰጡት አራት አማራጮች መካከል በየትኛው የሀሳብ ደረጃ ላይ እንደምትስማሙ ቁጥሮቹን በመክባብ አመልክቱ ።

| ተ.ቁ | ግለመር መማር ዛዴዎች | በጣም አልስማማም (1) | አልስማማም (2) | እስማማለሁ (3) | በጣም እስማማለሁ(4) |
|---|---|---|---|---|---|
| | ግብ ማስቀመጥ | | | | |
| 1 | በዚህ ክፍል ደረጃ ከሌሎች የበለጠ የአንብቦ መረዳት ችሎታ እንድኖረኝ እመኛለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 2 | በአማርኛ ትምህርት ክፍለ ጊዜ መምህሬ ሀሳቤን ተቀብሎ እንዲያስትፍ እፈልጋለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 3 | በሚማረዉ ትምህርት የተሸለዉን ብቃት እጠብቀለሁኝ | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 4 | ችሎታዩን ለማሻሸል የግሌን ጥራት አደረጋለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 5 | ግብ ማስቀመጤ የሚያነበዉን ምንባብ ትኩራት እንዲያይ አስችሎኛል፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 6 | የተሻለ ዉጤት ለማስመዝገብ አስተማሪ የሆኑ ተግባራትን ለማስራት እፈልጋለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 7 | መልመጃዎችን ስሰራ ስህተቴን ለማስተካከል ጥራት አደርጋለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 8 | በሌሎች ትምህርቶች በማንባብና በመማር የማገኛቸዉን ሀሰቦች በአንብቦ መረዳት ትምህርት ለመተግባር እሞክራለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 |
| | **የመማር ፍላጎት** | | | | |
| 9 | በአሁኑ ሰዓት በጣም የሚያስደስተኛ ነገር ዉጤት መግኘት ሳይሆን የአንብቦ መረዳት ችሎታየን ማሻሻል ነዉ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 10 | ለማንባብ ያቀድሁትን ከመጠነቀቄ በፊት የድካም ስሜት ሁሉ ጊዜ ይሳማኛል፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 11 | የተሻለ የሚሰራዉ ለጓዳኞቼ፣ ለወላዶቹ ወይም ለሌላ ለማሳየት አይደለም፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 12 | በሚማርበት ጊዜ ራሴን ለማበረታታት የሚችለዉን ያህል ጠንክሬ ለመስራት ጥራት አደርጋለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 13 | የመማሬን ግብ ለማሳከት ጥሩ ነገር በሥራሁ ጊዜ ሁሉ ለግሌ ማበረታቻ እስጣለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 14 | በትምህርት ክፍለ ጊዜ መምህሬ ጥንከሬዬንና ድክመቴን ላይቶ ሲጣቁመኝ ደስ ይለኛል፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 15 | የአንብቦ መረዳት ፈተና ጥሩ ዉጤት ስያስመዘግብ ሙሉነት ይሳመኛል፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 16 | በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የሚያረካኝ ነገር በቻልኩ መጣን የአንብቦ መረዳት ተግባራትን መስራት ነዉ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 |
| | **የመማር ዘዴዎች** | | | | |
| 17 | ችሎታዬን ለመዳባር በተለያየ መንገድ ደጋግሜ እሞክራለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 18 | መምህሩ በክፍለ የሚሰጠዉን ገለፃ ከሚያነበዉ ምንባብ ጋር በማዛመድ ሀሳቡን ለመረዳት እሞክራለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 19 | የምንባቡን አዳዲስ ፅንሳ ሀሳቦች በመዘርዘር ለማስታዋስ እሞክራለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 20 | የምንባቡን ፅንስ ሀሳቦች ካልገቡኝ ሌሎች ጓደኞቼን እጠይቃለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 21 | ምንባቡን ከነበብኩኝ በኋላ በፅሁፍ ዉስጥ ያሉ መረጃዎችን በጥልቀት መተንተን እና መገምገም እችላለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 22 | ምንባቡን ስያነብ የሚያጋጥሙኝን አደዲስ ቃላት ፍቺ በመፈለግና የቃል ክፍሉን በመመልከት ከአገባበቸዉ እገምታለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 23 | በመመሪያ ክፍልም ሆነ ወጪ ከቋንቋዉ ተናጋሪዎች ጋር በሚፈጥረዉ ግንኙነት የቋንቋ እዉቀት መነሳ ስሜት እንደይኖረኝ እንደቋንቋ ተማሪ ረሴን ለቷቷኂረዉ ቋንቋ ለሕብረተሰቡና ለባህሉ ቀና አመላካከት አሳያለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 24 | ምንባቡ ከበድ እየሆነ ሲመጠ የመረዳት ችሎታዬን ለማሳደግ ወደ ኋላ ተመልሼ አነባለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 |

# አባሪ ሁለት

## የአንብቦ መረዳት ችሎታ ፈተና

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂዩማኒቲስ የቋንቋዎች ጥናት የጆርናሊዝምና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ስነ-ፅሁፍና ፎክሎር ክፍል ትምህርት የድሕረ-ምረቃ መርሀ ግብር

ከዚህ በታች ከቀረቡት ምንባቦች የተዘገጁት የአንብቦ መረዳት ችሎታ ፈተናዎች፣ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የግለመር መማር ዘዴ ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያለው ተዛምዶ ለመፈተሽ ለሚካሄድ ጥናት መረጃ ለመሰብሰቢ ተስቦ የተዘገጃና በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የሚመለሱ ናቸው፡፡

የፈተናው ዋና ግቡ አንተ/አንቺ መረጃ ሰጪ ተማሪ በአማርኛ ቋንቋ የቀረቡ ፅሁፎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ምን እንደሚመስል ለመረዳትና ከግለመር መማር ዘዴ ጋር ያለውን ተዛምዶ ለመፈተሽ ነው፡፡ የሚሰበሰበው መረጃ ከምርምሩ አላማ ሌላ ምንም ተግባር የለም፡፡

1. የክፍል ደረጃ..................
2. የአፍ መፍቻ ቋንቋ .........
3. ፆታ፦ወ......ሴ......ድ............

አቅጣጫ፦ ውድ ተማሪዎች ከዚህ በታች ሁለት የተለያዩ ምንባቦች አሉ፡፡ ከምንባቡ ውስጥ ሃያ ጥያቄዎች አሉ፡፡ አንደኛው ምንባብ አስር ጥያቄዎች ይዟል፡፡ ከእነዚህ ሰባቱ ጥያቄዎች አማራጭ  መልሶችን አራት ያለው ሲሆኑ ሶስቱ አጭር መልስ የሚሰጥባቸው ናቸው፡፡ የሁለተኛው ምንባብ አስር ጥያቄዎች የተዘገጁ ሲሆን አምስቱ ጥያቄዎች ሁለት  አማራጭ መልስች እንዲሁም ሶስት ጥያቄዎች ደግሞ ብዙ አማራጭ መልሶች የሏቸው ናቸው፡፡ ሌሎቹ ጥያቄዎች አጭር ምለሽ የሚሰጥባቸው ናቸው፡፡ ምንባቡን በጥንቃቄ ካነባብክ / ካነባቢሽ በኋላ ትክክለኛ የሚትለውን/የምትይው መልስ መልስመስጫ ቦታ ላይ አስቀምጥ /አስቀምጪ፡፡ በትኩረት ማንባብና ትክክለኛውን መልስ መስጣት ለሚሰራው ጥናታዊ ፅሁፍ በጎ የሆነ አስተዋፅኦ አለው፡፡ በመሆኑም ጥናቱ የታለመለትን ግብ የሚመተው በሚትሰጡት ትክክለኛ መልስ በመሆኑ ጥያቄዎቹ ምለሽ በሚያገኙበት ጊዜ ትክክለኛውን የግለችሁን ሀሳብ ብቻ የሚወክለውን ምላሽ እንዲትሰጡ በአክብሮት እጠይቃለሁኝ፡፡

**ግንዘቤ**

በወረቀት ላይ ስማችሁን አትፃፉ፡፡

የፈተና መልስ ሚስጢር ይጠበቃል፡፡

ፈተናውንከጨረሳቹሁ በኋላ ወረቀቱን ለሰጣችሁ ሰው መልሱ፡፡

# ምንባብ አንድ

ቆሻሸ ከመኖሪያ ቤታችን፣ ከቢሮዎችና ከእንዱስትሪዎች እያወጣን የምንጥለው የማይፈለግ ነገር ነው። ቆሻሸ ሲባል በየቦታው ተዝረክርኮ ወይም በየቆሻሸ መጣያ ቅርጫት ውስጥ ያለ አለዚያም እርጥብ የእንዱስትሪ ቆሻሸ ሊሆን ይችላል። ሁላችንም ቁርጥራጭ ወረቀቶችን፣ የምግብ ትራፊዎችን ወይም ሌሎች ነገሮችን በምንጥልበት ወቅት ቆሻሸ እንፈጥራለን። የእንዱስቱሪ ምርቶች በሚመረቱበት ጊዜም ቆሻሸ ይፈጠራል። ቆሻሸ ቁጥጥር ካልተደረገበትና በማንኛውም ቦታ የሚጣል ከሆነ፣ በአካባቢና በሰው ላይ ጉዳት ሊያስከትል ይችላል። ስለዚህም፣አፈርን ወይም ውሃ ማይበክልበት ቦታና ሰዎችም በዚሁ ሳቢያ ለአደጋ በማይጋለጡበት ሁኔታ ማስወገድ አለብን። ማንኛውም የቆሻሸ አይነት በአግባቡ ካልተያዘ አኛንና አካባቢን ሊጎዳ ይችላል፣ አካባቢን እይታ ያበላሻል፣መጥፎ ጠረን ያስከትላል።ለዝንቦች፣ለአይጦችና ልዩ ልዩ ተዋህስያን መራቢያ በመሆን በሽታ እንዲሰራጭ ያደርጋል። ዕፅዋትን፣እንስሳትንና ሰዎችን ይመርዛል። አየርና ውሃን ይበክላል።

የረጅም ጊዜጎጂ ተፅኖው ደግሞ መርዛማ ኬሚካሎች በአካባቢው ውስጥ ሳይሰባበሩ መቆየታቸውና በአየርና በተፈጥሮ ሀብቶች ላይ ጉዳት ማድረሳቸው ነው።

ሁላችንም ብንሆን በቀጥተም ሆነ በተዘዋዋሪ ቆሻሸ ስለምንፈጥርና ይህም ቆሻሸ ብክላትን ስለሚያስከትል፣ በአግባቡ የመያዝ ኃላፊነት አለብን።

የቆሻሸ አያያዝ በአራት ደረጃዎች ካሄዳል። ይህም የተቀናጃ የቆሻሸ አያያዝ ይባላል። የመጀመሪያው ደረጃ እንዱስትሪዎች በተቻለ መጠን አነስተኛ ቆሻሸ የሚፈጥሩበትን አመራረት ሂደት መከተላቸውነው። ይህ በንፁህ የአመራረት ሂደት መጠቀም ይባላል። ሁለተኛው እርምጃ ተመልሶ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችለውን ማንኛውንም ነገር ከቆሻሸ መለየት ነው። ይህ ቆሻሸን መልሶ መጠቀም ወይም ሀብት እንዲያገግም ማድረግ ይባላል። ሶስተኛው እርምጃ እያንዳዱን የቆሻሸ አይነት አነስተኛ ቦታ እንዲይዝ አድርጎ ማጨቅና ጉዳቱ እንዲቀንስ ማጣራትነው። አራተኛው እርምጃ ከላይ የተጠቀሱት ተግባሮች ከተከናውኑ በኂላ የሚቀረውን ማንኛውንም ቆሻሸ በአግባቡ ተጠንቶ ወደ ተሰራ የቆሻሸ መጣያ ወስዶ መጣል ነው።

ከላይ በተጠቀሱት መንገዶች ቆሻሸን ከምንጩ ጀምሮ እስከምወገድበት ስፍራ ድረስ የሚደረግ ክንውን፣ ቆሻሸን ከምንጩ እስከመቀበሪያው የመቆጣጠር መርሆ ይባላል። ይህንን መርሆ በመተግበር የምናልመውን ንፁህ አካባቢ መፍጠር ፋይዳው ብዙ ነውና ዛሬውኑ ለተግባር እንነሳ።

**ምንጭ፦** 9ኛክፍልአማርኛየተማሪውመፅሐፍ፣ 2004 ፣122

*መመሪያ አንድ፦ከተራቁጥር1-7 ድረስ የቀረቡት ጥያቄዎች ምንባብን መሠረት ያደረጉ የምርጫ ጥያቄዎች ስለሆኑ ከቀራቡት አማራጮች መካከል ትክክለኛ መልስ የያዘውን ሆሄ በመምረጥ መልስ መስጫ ወረቀት ላይ ፃፍ / ፃፊ።*

1 . የምንባቡ ዋና መልዕክት ምንድነው ?

ሀ / ማንኛውም ቆሻሻ በአግባቡ ከልተያዘ ሰውንና አካባቢን ይጎደል

ለ / ሁላችንም በቀጥተም ሆነ በተዘዋዋር ቆሻሻን እንፈጥራለን

ሐ / የቆሻሻ አያያዝ አራት ደረጃዎች አሉት

መ /ቆሻሻን መልሶ መጠቀም ከፍተኛ ጥቅም አለው

2 . ከሚከተሉት መካከል ከምንባቡ ሀሳብ ጋር የማይዛመድ መልዕክት የያዘው አ . ነገር የቱ ነው ?

ሀ/ቆሻሻ በተቀናጃ ሁኔታ መያዝ አለበት ለ/ቆሻሻ የረጅም ጊዜ ጎጂ ተፅኖ ያመጣል ሐ / ቆሻሻ በጤና ላይ ብዙም እክል አያስከትልም መ/ ሀናለ መልስናቸው

3 . ቆሻሻን በጥናት ወደ ተሰራ መጣያ ወስደን ከመጣላችን በፊት መከነወን ያለበት ተግባር የትኛውነው ?

ሀ/ማጫቅናማጣራት / ሐ በንፁህ የአመራረት ሂደት መጠቀም

ለ / ሀብትእንዲያጋግምማድረግ መ/ መልስ አልተሰጠም

4 . በአግባቡ ያልተያዘ ቆሻሻ በሽታን እንዲሰራጭ የሚያደርገው በምንድነው ?

ሀ / መጥፎ ጠረን በመምጠት ለ/ የአካባቢ እይታን በመበለሻት ሐ/ የልዩ ልዩ ተዋህሳያን መረቢያ በመሆን መ/ሁለም

5 .በጥቅም ላይ ሊሆን የሚሆን ነገር፣ ከቆሻሻ መለየት …………ይባላል።

ሀ/ ማጣራት ለ /ሀብትን እንዲያጋግም ማድረግ

ሐ / ከብካለመፅዳትመ /ምርትንመልሶመጠቀም

6 . ከሚከተሉት መካከል ለምንባቡ ርዕስ ሊሆን የሚችለው የቱነው ?

ሀ / ቆሻሸይጎዳልለ/ ቆሻሻናአወጋገዱሐ/ አካባብመጠበቅመ/ ቆሻሻናአይነቱ

7 ."ፋይደ"ለሚለውቃልበፍችየማይመሳሰለውየቱነው ?

ሀ / ውጤትለ / ጥቅምሐ / ሁኔታመ / ፍቺ

መመሪያ ሁለት፦ከላይ የቀረበውን ምንባብ በማንባብ ከተራ ቁጥር 8 - 10. ያለውን ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጥ / ጪ

8 .ማንኛውም ቆሻሻ በአግባቡ ከልተያዘ ምን ይጎዳል?

9. ለኑሮ ምቹ አካባቢ ለመፍጠር ዋና መሰረት ምንድነው ?

10. በምንባቡ ውስጥ የቆሻሻ አወጋገድ ደረጃዎች እነማን ናቸው ?

መልስ የሚሰጥበት ወረቀት

ከፍ ብለው ለቀረቡት ጥያቄዎች በሚከተለው መልስ መስጫ ወረቀት በትዕዛዛቸው መሠረት መልስ ስጡ፡፡

ክፍል .........መማሪያ ክፍል...... መለያ ቁጥር......

መመሪያአንድ፦ምርጫ

1 ...........................

2...........................

3...........................

4.........................

5.........................

6..........................

7..........................

መመሪያሁለት፦አጭርመልስስጡ

8.........................................................................................................

9.........................................................................................................

10.......................................................................................................

## ምንባብ ሁለት

ኢትዮጵያ በብዙ ታሪክ ፀሐፊዎች የተደነቀ ረጅምና አኩሪ ታሪክ ያላት ሀገር ናት፡፡ ታዋቂነት ያላት ሀገራችን በዘመናት ታሪኳ ውስጥ ብዙ ወጣ ወረድና ፈተና ደርሶባታል፡፡ ይሁን እንጅ በአባቶቻችንና በናቶቻችን ያልተቋረጠ ተጋድሎ ህልውናዋ ተጠብቆኖሯል፡፡

በጀግንነትና በመስዋዕትነት ያጌጠው የኢትዮጵያ የነፃነት ታሪክ ተከብሮ መኖር ሲተወስ፤ ምንጊዜውም መዘጋት የሌለበት ጉዳይ ሁኔታው የእድል ወይም የአጋጣሚ ሳይሆን የሰፊው ህዝብ ጀግንነትና መሰዋዕትነት ውጤት መሆኑ ነው፡፡ ኢትዮጵያ በረዥሙ ታሪኳ ውስጥ ያለፈችባቸው በተጋድሎ የተሞሉ ትግሎች ሁሉ ነጻነቷንና ሉአላዊነቷን ለመጠበቅ እንጅ የሌሎችን ግዛትና አንድነት ለመድፈር አይደለም፡፡ የሌሎችን ያለመመኘቷን ያህል ግን ሌሎች እጃቸውን አልሰበሰቡም፡፡ ሀገራችን የጠላቶቿ የትኩረት ኢላማ ካደረጓት ልዩ ልዩ

ምክንያቶች መካከል አንዱ የተፈጥሮ ሀብቷና ውበቷ ሲሆን ሌላው ደግሞ የምትገኝበት አካባቢ ስትራቴጂያዊነት ነው።

ኢትዮጵያ በአባይ ሸለቆ መካከል ቁልፍ ስፍራ ይዛ ትገኛለች። የውጭ ሀይሎች ያለማቋረጥ ሲነሱቢን የኖሩትም ይህን አንዱን መሰረታዊ ሁኔታ ምክንያት በማድረግና ለመቆጣጠር በመፈለግ እንደሆነ ይታወቀል። ይሁን እንጂ ላገራችን ያለንን እጅግ ጥልቅ ፍቅር ተቋቁመናል፤ በመቋቋም ላይም እንገኛለን። የተሰነዘሩብን ተደጋጋም ጥቃቶች የቁጭትና የአትንኩኝነት መንፈሳችንን አጠናከሩት እንጂ እንድንበገር አላደረጉንም። ለዚህም በተደጋጋሚ የተቀዳጀ ናቸው ድሎች ምስክሮች ናቸው።

ካንድምዕተ አመት በፊት ካፒታሊዝምበ አውሮፓ ዳብሮ ሌሎች ሀገሮችን በቅኝ ግዛትነት ለመቀራመመት በተጠናከረ መንገድ ተንቀሳቅሶ በተለይም አፍሪካን ኢላማው አድርጎ እንደነበረ ይታወሳል። በዚሁ ጊዜ ኢትዮጵያ ለቅኝ ግዛትነት ከተተኮረረባቸው ሀገሮች አንዷ ነበረች።

በ1869እ.ኤ .አ የስዊዝ ቦይ መከፈት የቀይ ባህር አካባቢን ጠቀሜታ ስላጎላው የወቅቱን ሃያላን መንግስታት ትኩረት ስቧል።

ያየታሪክ ወቅት በዘመነ መሳፍንት ተዳክሞ የነበረውን የኢትዮጵያ መንግስት የማማከል ሂደት በአጼቴዎድሮስ ተጀምሮ በአጼዩሐንስ የተጠናከረበትነ በር። ይህም የማዕከላዊ መንግስት እየተጠናከረ መምጣት በተደጋጋሚ የተሰነዘሩትን ጥቃቶች ለመከላከል ወሳኝ አስተዋፅኦ አድርጓል።

ምንጭ፦ብርሃኑ / ጻድቅ፣ 2010 ፣539 -540

መመሪያ አንድ፦ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በደንብ ካነባበችሁ በኃላ ጥያቄዎቹ የያዙት ሀሳብ ትክክል ከሆነ"እውነት"ስህተት ከሆኑደግሞ"ሀሰት"በማለት መልሱ።

1 . ኢትዮጵያ የተደነቀ ረጅምና ባለብዙ ታሪክ ያላት ሀገር ነት።

2 . የኢትዮጵያ የነፃነት ታሪክ ተከብሮ መኖር መነሻው ሲተዋስ ጀግንነትና መስዋዕት አይደለም።

3 . ኢትዮጵያ በተደጋጋም የተቀዳጀችው ድሎች ቢኖሯትም መሸነፍ አልቻላችም።

4 .በአጼቴዎድሮስ ዘመን መንግሥት የኢትዮጵያ መንግስት የማማከል ሂደት አልተጀመረም።

5 .ኢትዮጵያ ለቀኝ ግዛትነት ከልተገዙ ሀገሮች አንዷ ነበረች።

መመሪያ ሁለት፦ ከዚህ በታች በ"ሀ" ስር ለቀረቡት ቃላት በ"ለ" ስር ከቀረቡት ጋር የሚስማማውን በመፈለግ አዛምዱ።

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 6 . ሉአላዊነቷን | ሀ / ሕይወት መስጠት |
| 7 . መስዋዕትነት | ለ /ጉብዝና |
| 8. ጀግንነት | ሐ / የሀገር ክብሩን |
| | መ / ፍሪሃት |
| | ሠ/ ተዋርዶ |

መመሪያ ሶስት፦ ከታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ምንባቡ በመሰረት አጭር መልስ ስጡ።

9 . ኢትዮጵያን በተደጋጋሚ ሃያላን መንግሥታት ለምን ይፈልጋሉ?

10 .ካፒታሊዝም በአውሮፓ በመዳበር ሌሎች ሀገሪትን ምን ሊያደሪግ ነበረ?

የመልስ ወረቀት

መለያቁጥር.........ክፍል.........መመሪያክፍል............

መመሪያአንድ፦ እውነትወይምሀሰት

1…………………………………...

2…………..................................

3…………..................................

4…………..................................

5……......................................

መመሪያሁለት፦አዛምድ

6….......................................

7….......................................

8….........................................

መመሪያ ሶስት፦አጭር መልስ

9………………………………………………...........................................................

10…………………………………………………......................................................

## አባሪ ሶስት

| | | የጽሑፍ መጠይቅ ፈተና | | |
|---|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | አንብቦ መረዳት ፈተና | ግብ ማስቀመጥ | የመማር ፍላጎት | የመማር ዘዴ |
| 1. | 17 | 22 | 21 | 21 |
| 2. | 75 | 25 | 29 | 28 |
| 3. | 93 | 29 | 29 | 29 |
| 4. | 85 | 28 | 28 | 29 |
| 5. | 77 | 27 | 28 | 28 |
| 6. | 85 | 29 | 29 | 29 |
| 7. | 97 | 29 | 29 | 28 |
| 8. | 87 | 28 | 29 | 27 |
| 9. | 75 | 26 | 27 | 28 |
| 10. | 85 | 29 | 26 | 29 |
| 11. | 78 | 27 | 28 | 28 |
| 12. | 65 | 28 | 25 | 29 |
| 13. | 85 | 27 | 28 | 28 |
| 14. | 75 | 29 | 26 | 29 |
| 15. | 80 | 29 | 27 | 29 |
| 16. | 90 | 28 | 26 | 27 |
| 17. | 85 | 29 | 29 | 29 |
| 18. | 75 | 29 | 28 | 29 |
| 19. | 95 | 28 | 29 | 27 |
| 20. | 78 | 29 | 28 | 29 |
| 21. | 80 | 29 | 28 | 29 |
| 22. | 70 | 27 | 29 | 28 |
| 23. | 65 | 26 | 26 | 27 |
| 24. | 85 | 25 | 26 | 24 |
| 25. | 90 | 26 | 28 | 27 |
| 26. | 18 | 20 | 20 | 21 |
| 27. | 85 | 28 | 27 | 29 |
| 28. | 38 | 24 | 28 | 22 |
| 29. | 80 | 23 | 27 | 28 |
| 30. | 60 | 28 | 28 | 29 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 31. | 70 | 26 | 26 | 27 |
| 32. | 60 | 28 | 29 | 28 |
| 33. | 61 | 27 | 28 | 27 |
| 34. | 70 | 28 | 26 | 29 |
| 35. | 85 | 27 | 27 | 27 |
| 36. | 75 | 25 | 28 | 24 |
| 37. | 81 | 27 | 28 | 29 |
| 38. | 70 | 29 | 27 | 26 |
| 39. | 60 | 29 | 29 | 29 |
| 40. | 80 | 25 | 26 | 26 |
| 41. | 70 | 27 | 28 | 29 |
| 42. | 66 | 27 | 27 | 27 |
| 43. | 65 | 27 | 27 | 29 |
| 44. | 61 | 26 | 26 | 26 |
| 45. | 79 | 27 | 28 | 29 |
| 46. | 70 | 26 | 26 | 26 |
| 47. | 42 | 24 | 27 | 27 |
| 48. | 70 | 25 | 28 | 27 |
| 49. | 85 | 20 | 29 | 28 |
| 50. | 80 | 26 | 26 | 27 |
| 51. | 67 | 24 | 28 | 24 |
| 52. | 70 | 22 | 26 | 28 |
| 53. | 79 | 27 | 27 | 29 |
| 54. | 80 | 23 | 23 | 27 |
| 55. | 70 | 27 | 28 | 29 |
| 56. | 65 | 26 | 29 | 27 |
| 57. | 19 | 23 | 21 | 22 |
| 58. | 91 | 29 | 29 | 29 |
| 59. | 75 | 27 | 27 | 28 |
| 60. | 20 | 20 | 20 | 20 |